# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 080 ኅዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ርዳታ ተሰጥቷል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት በጎርፍ፣ በግጭትና በድርቅ ለተጎዱ 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች በሁለት ዙር 7 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር ወጪ በማድረግ ርዳታ ማድረሱን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች በርካታ ሰዎች ተፈናቅለው ይገኛሉ፡፡

ክልሎች የቅድሚያ ቅድሚያ የሚያስፈልጋቸውን በጎርፍ፣ በድርቅና በግጭት የተፈናቀሉ ዜጎችን በመለየት ባሳወቁት መሠረት መንግሥት ከሁለት ሳምንት በፊት ሁለተኛ ዙር የምግብ ርዳታ ማድረሱን አቶ አታለለ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ አታለለ ገለጻ፤ መንግሥት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለርዳታ ፈላጊዎች በአርባ አምስት ቀን ልዩነት በሁለት ዙር ለ 7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ርዳታ ማድረሱን ጠቁመው፤ በዚህም መሠረት በሰሜን ጎንደር፣ በዋግህምራና በትግራይ ክልል ሶስት ዞኖች በተከሰተው ድርቅ ጉዳት ለደረሰባቸው

ብሔራዊ ባንክ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## ‹‹አመራሩ የሕዝቡን ርካታ ለማረጋገጥ ውጤት በሚያስገኝ መልኩ መትጋት አለበት››

- አቶ አደም ፋራህ
የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አመራሩ የሕዝቡን ርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ ውጤት ለማምጣት መትጋት እንዳለበት የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ አደም ፋራህ ገለጹ፡፡

ምክትል ፕሬዚዳንቱ ትናንት በጎንደር የሥልጠና

‹‹አመራሩ የሕዝቡን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## መንግሥት
# ለአፈር ማዳበሪያ የ52 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል

- ከ14 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ለአፈር ማዳበሪያ የ52 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉ ተገለጸ። ለ2016/17 የምርት ዘመን እስካሁን ከ14 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል።

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶክተር) የ2016/17 የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትን አስመልክተው ትናንት በሰጡት መግለጫ፣ መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የማዳበሪያ ዋጋ ጭማሪ ቢኖርም የአርሶና ከፊል አርብቶ አደሮችን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ ከፍተኛ ድጎማ እያደረገ ይገኛል። በዚህም ባለፉት ሶስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ የ52 ቢሊዮን ብር ድጎማ ማድረጉን አስታውቀዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ ላለፉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ ጨምሯል። መንግሥት የአርሶ አደሩን የመግዛት አቅም

መንግሥት ለአፈር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

ሶፊያ ካሳ (ዶክተር)

# ብሔራዊ ባንክ
## የዋጋ ግሽበትን ለማረጋጋት በትኩረት እንዲሠራ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ ብሔራዊ ባንክ የወሰዳቸው ጥብቅ የፊሲካል ፖሊሲ ርምጃዎች ውጤት ቢያስገኙም ከሚታየው ችግር አንጻር ትኩረት እንዲሰጠው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ፡፡

ቋሚ ኮሚቴው ትናንት የብሔራዊ ባንክን የ2016 ዓ.ም ሩብ ዓመት አፈጻጸም ገምግሟል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ደሳለኝ ወዳጆ የዋጋ ንረቱ ባለበት እንዲቆምና እንዲረጋጋ እንዲሁም የበጀት ጉድለትን ለመሙላት የግምጃ ቤት ሰነድ በመሸጥ ገንዘብ

ብሔራዊ ባንክ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## በአምስት ዓመታት ለሁሉም መምህራን ሥልጠና በመስጠት ሰርቲፋይድ ለማድረግ እየተሠራ ነው

- 5 ሺህ የትምህርት አመራሮች ሥልጠና ወስደው ሰርቲፋይድ ሆነዋል

ገጽ 3







# ኮሌጆቹ ከ33 ሺህ በላይ አዳዲስ ሠልጣኞችን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል

**ቃልኪዳን አሳዩ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ኮሌጆች በዘንድሮው የትምህርት ዘመን 33 ሺህ 766 አዳዲስ ሠልጣኞችን ለመቀበል ዝግጅት ማድረጋቸውን የአዲስአበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ መክበብ ወልደሃና እንደተናገሩት፤ በቢሮው ስሩ በሚገኙ 15 ኮሌጆች ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አምስት ድረስ በ 123 የተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሥልጠናዎች ይሰጣሉ። ኮሌጆቹ በዘንድሮ ትምህርት ዘመን ከ33 ሺህ በላይ አዳዲስ ሠልጣኞችን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል፡፡

ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠናው የሚያስፈልጉ የወርክ ሾፕ፣ የግብዓትና የአሠልጣኞች ዝግጅት መደረጉን አመልክተው፤ የተለያዩ ኮሌጆች ተማሪዎችን በመመዝገብ በክህሎት የዳበረ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም የሠልጣኞች ምዝገባ በቅስቀሳ ይከናወን እንደነበረ አቶ መክበብ አስታወሰው፤ አሁን በበይነ መረብ እገዛ ምዝገባውን በማከናወን ኮሌጆች ተቀብሎ እያሠለጠኗቸው ከሚገኙ ነባር 11 ሺህ ሠልጣኞች በተጨማሪ በዘንድሮው የትምህርት ዘመን ከ33 ሺህ በላይ አዳዲስ ሠልጣኞችን ለመቀበል በየኮሌጆቹ ምዝገባ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

በምዝገባ ሂደቱ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመግባት የሚያስችል ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበው ምርጫቸውን ወደ ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛዎች ያደረጉ ወጣቶች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

በዝግጅት ምዕራፍ ሥራዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ የመማሪያ ክፍልና መግቢያዎች፣ የመጸዳጃ ቤቶች፣ ቤተ ሙከራዎችና የተለያዩ መገልገያዎችን ዝግጁ መደረጋቸውን ጠቁመዋል፡፡

ማሰልጠን ብቻ ግብ አይደለም ያሉት አቶ መክበብ፤ ሥልጠናውን በጥራት ከመስጠት በተጨማሪ ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር በተሠራው ሥራ በቅርቡ 20 ሺህ ወጣቶች ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል ብለዋል።

ከመዲናዋ የሥራ የኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ወጣቶችን የማደራጀት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

አዲስ አበባ ተግባረ ዕድ፣ እንጦጦ ፖሊ-ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ጄነራል ዊንጌትና ሌሎች ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች የተሻለ የሥራ ሃሳብ ያላቸውን 140 ወጣቶች በስድስት ኢንተርፕራይዞች በማደራጀት የገንዘብና የመሥሪያ ቦታ ድጋፍ በማቅረብ ወደ ገበያ እንዲገቡ ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

ቴክኒክና ሙያ ተቋማት በአካባቢያቸው ያለውን ጸጋ መሠረት አድርገው ሥልጠና እንዲሰጡ እየተደረገ መሆኑን አንስተው፤ አዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአካባቢው የተለያዩ የመንግሥትና የግል ሆስፒታሎች ስለሚገኙ የባዮ ሜዲካል ሙያ ዘርፍ ላይ በተሻለ ሁኔታ ሥልጠና እየሰጠ መሆኑን ገልጸዋል።

የንፋስ ስልክ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ደግሞ በዙሪያው የተለያዩ የተሽከርካሪ ኩባንያዎች ስለሚገኙ የአውቶሞቲቭ ዘርፍ ሥልጠናዎችን በስፋት እየሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።



**አቶ መክበብ ወልደሃና**

ወጣቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሚሰጡት ግምት እየተሻሻለ መምጣቱን አስታውቀው፤ ለሙያ ትምህርቶች ያለው ግንዛቤ እንዲያድግ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

ቴክኒክና ሙያ ተቋማት አማራጭ ሳይሆኑ ተቀዳሚ ምርጫ በመሆን ተማሪዎች ውጤት ስላልመጣላቸው ብቻ ሳይሆን ተገቢውን ክህሎት ለመጨበጥ የሚያስችሉ የትምህርት ተቋማት መሆናቸውን ተናግረዋል።



# በስልጤ ዞን ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ የሚያስገኝ የሮዝመሪ ምርት ይጠበቃል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በዞኑ ለውጭ ገበያ በመቅረብ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የሚያስገኝ የሮዝመሪ ምርት ለማግኘት መታቀዱን የስልጤ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡ ከምርት ዘመኑ 75 ሺህ ኩንታል የሮዝመሪ ምርት እንደሚጠበቅም ተገልጿል፡፡

የስልጤ ዞን ምክትል አስተዳዳሪና የግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙርሰል አማን ለኢፕድ እንደገለጹት ፤ በምርት ዘመኑ በሦስት ሺህ ሄክታር መሬት ላይ ከለማው የሮዝመሪን ሰብል 75 ሺህ ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

በዞኑ ከሚለማው የሮዝመሪን ምርት ከ20 ሺህ ኩንታል በላይ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ሙርሰል፤ ከወጪ ንግዱ ከሦስት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በዞኑ የሮዝመሪ ምርት በስፋት በመልማት ላይ በመሆኑ ወደ አረብና የተለያዩ የእስያ ሀገራት እየተላከ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ዘንድሮ ወደ አውሮፓ ሀገራት ለመላክ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በ2015 ምርት ዘመን ከተመረተው 50 ሺህ ኩንታል የሮዝመሪ ምርት 13 ሺህ 800 ኩንታሉ ለውጭ ገበያ መቅረቡን ጠቅሰው፤ ከዚህም ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን አስታውሰዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እየተሰበሰበ የሚገኘውን የሮዝመሪን ምርት በጥራት አድርቆ በማዘጋጀት ለአውሮፓ ገበያ ለማቅረብ እየተሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ጊዜ የገበያ መዳረሻዎች የማስፋት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን አስረድተዋል።

በዞኑ የሚገኙ አምስት ወረዳዎችና የወራቤ ከተማ አስተዳደር በሮዝመሪ ምርት ላይ በስፋት እየተሳተፉ መሆናቸውን ገልጸው፤ በይበልጥ በደጋ አካባቢዎች ላይ በስፋት የማልማት ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል፡፡

ከ12 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች በሮዝመሪ ምርት ተሳታፊ መሆናቸውን አስታውቀው፤ አርሶ አደሩ ከምርቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት አማራጭ እየሰፋ መምጣቱን ገልጸዋል።

የአፈር አሲዳማነት በሚታይባቸውና በደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎች ላይ በስፋት እየለማ ለገበያ እየቀረበ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ለአርሶ አደሩ የገበያ ትስስርን በመፍጠርና የወቅቱን የገበያ መረጃ በማቅረብ ከምርት ላኪዎች ጋር በጋራ እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሙርሰል፤ አርሶ አደሩን በመሠረታዊ የህብረት ሥራ ማህበራት በማደረጃት ውጤታማ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

የሮዝመሪ ምርት ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር የአካባቢ መራቆትንና የአፈር መሸርሸርን ለማከላከል የሚረዳ መሆኑን አስገንዝበዋል።

# አገልግሎቱ የስታትስቲክስ መረጃ ፍላጎትን ለማሟላት ሪፎርም እየሠራ ነው

## - 5ኛው የኢትዮጵያ ሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት ዘንድሮ ይካሄዳል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የሥነ-ሕዝብ ለውጦች ተከትሎ እያደገ የመጣውን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎትን ለማሟላት የሪፎርም ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ አገልግሎት አስታወቀ። የኢትዮጵያ ሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት በተያዘው ዓመት ለአምስተኛ ጊዜ እንደሚካሄድ ተመላክቷል።

የኢትዮጵያ ስታስቲክስ አገልግሎት ከአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን ስታቲስቲክስ ዲፓርትመንት ጋር በመተባበር የ2016 ዓ.ም የአፍሪካ የስታቲስቲክስ ቀን ሰሞኑን አከብሯል።

የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሙሉቀን ቀሬ በወቅቱ ባደረጉት ንግግር እንዳስታወቁት፤ የሀገሪቱን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የሥነ-ሕዝብ ለውጦችን ተከትሎ እያደገ የመጣውን የሀገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት ለማሟላት ሁሉን አቀፍ የሪፎርም ሥራ እየተሠራ ነው።

ከባለፈው ዓመት ጀምሮ የአመራር፣ የአደረጃጀትና ሌሎች ተግባራትን ያካተተ የሪፎርም ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ሙሉቀን፤ የሀገሪቱን የአሁንና የቀጣይ ጊዜያት የስታቲስቲክስ የመረጃ ፍላጎት መመለስ የሚያስችል የሰው ኃይል አቅም ግንባታና ስምሪት፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና አስቻይ ቴክኖሎጂን አሟጦ መጠቀም በሪፎርም ሥራው ላይ እየተተገበሩ ከሚገኙት መካከል መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋፋት፣ የስታቲስቲክስ መረጃ ሰጪዎችን ግንዛቤ በማሳደግ ተባባሪ ማህበረሰብን በመፍጠር የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የሥነሕዝብ ስታትስቲክስ መረጃ አቅርቦት ጥራትና ተደራሽነትን መጨመር ዓላማ ያደረገ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ሥነ-ሕዝብ ጤና ጥናት በተያዘው ዓመት ለአምስተኛ ጊዜ ለማካሄድ በቂ ዝግጅት መደረጉን ገልፀው፤ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ባለሙያዎች በሚቀጥሉት ወራት ይሰማራሉ ብለዋል። መረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ዜጎች ተገቢውን ትብብር እንዲያደርጉም አሳስበዋል።

የግብርና ቆጠራ ዝግጅትም በተያዘው ዓመት የሚጀምር ሲሆን፤ በርካታ ሥራዎችን የሚጠይቅ በመሆኑ ሁለት ዓመት የሚደርስ የዝግጅት ጊዜ ይጠይቃል ብለዋል።

ለጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን የማሰባሰብ ሂደት አድካሚ በመሆኑና ሠራተኞች ቶሎ ቶሎ ሥራ መልቀቃቸው ተግዳሮት መሆኑን አስረድተዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ቆጠራ፣ አምስተኛ ዙር የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብና ጤና ጥናት፣ ሁለተኛ ዙር የግብርና ቆጠራ እና ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀናጀ የቤተሰብ ፍጆታ ጥናት በቀጣይ ሶስት ዓመታት በስታትስቲክስ ልማት ፕሮግራም የሚተገበሩ መሆናቸውን አመላክተዋል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ጥሩማር አባተ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ስታቲስቲክስ አገልግሎት ሀገሪቱ እያከናወነችው ላለው የሪፎርም ሥራ፣ ለፖሊሲ አውጪዎችና ለውሳኔ ሰጪ አካላት ታማኝነት ያለውን መረጃ በመሰብሰብ ተደራሽ እያደረገ የሚገኝ ተቋም ነው።

የ2016 ዓ.ም የአፍሪካ የስታትስቲክስ ቀን የስታስታትክስ መረጃን ማዘመን ለአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ ንግድ ቀጣና ትግበራ ያለው ሚና በሚል ሃሳብ በትናንትናው ዕለት የተከበረ ሲሆን፤ ቀኑ መከበሩ ልምድና ተመክሮዎችን ለመለዋወጥ እና የሀገሪቱ የመረጃ ፍላጎት ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ይረዳል ተብሏል።

# በገጠር የመጋዘን አለመኖር ለምርት ብክነት አንዱ መንስኤ ነው

**ምሕረት ሞገስ**

አዲስ አበባ፡- ለአርሶ አደሩ ቅርብ የሆነ የእህል ማከማቻ መዋቅር አለመኖር ለምርት ብክነት መንስኤ እየሆነ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ የብድር አቅርቦት ችግርም ለዘርፉ ማነቆ መሆኑ ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር) በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በገጠር የማከማቻ መጋዘን ባለመኖሩ አርሶ አደሩ ጊዜ እና ጉልበት አፍስሶ ያመረተው ምርት እየባከነ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይህ አርሶ አደሩን ብቻ ሳይሆን ሸማቹንም እየጎዳ፤ በገበያ ላይ የአቅርቦት እጥረት እንዲፈጠር እያደረገ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

ሸማቹ በተለይ የሠብል ምርትን በተጋነነ ዋጋ እንዲገዛ ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ የአቅርቦት ማነስ መሆኑን የተናገሩት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የማከማቻ መዋቅር አለመኖር የአምራቹን፣ የአርሶ አደሩን እና የሸማቹን ብቻ ሳይሆን በአጠቃለይ በሀገር ምርት ላይ እየፈጠረ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አለመሆኑንም አመላክተዋል፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል ከመንግሥት በተጨማሪ የግል ዘርፍ ባለሀብቶችም በከተማ ሆቴል ግንባታ ላይ ከመረባረብ ይልቅ፤ በዋናነት የግብርናውን ችግር የሚያቃልል የማከማቻ መጋዘን መገንባት ላይ ቢሠማሩ በሀገሪቱ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይቻላሉ በማለት ለባለሀብቶች ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከማከማቻ መዋቅር በተጨማሪ ሌላኛው የግብርናው ዘርፍ ችግር ፋይናንስ መሆኑን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ባንኮች አጠቃላይ ስሪታቸው ከተማ ላይ መሆኑን በማስታወስ፤ ገጠሩን ለማልማት ለረዥም ጊዜ የሚሆን ገንዘብ የሚያበድሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንዳለባቸው አስታውቀዋል፡፡

« ባንኮች ዋስትና ይፈልጋሉ፡፡ አብዛኛው አርሶ አደሩ ያለው የሣር ቤት እና በሬ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለባንክ ዋስትና አይሆንም፡፡» ያሉት ማንደፍሮ (ዶ/ር)፤ በዚህ ሳቢያ አርሶ አደሩ በብድር ተደራጅቶ ትራክተር የሚያገኝበት እና ምርታማነቱም ሀገር ከማጥገብ አልፎ በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥ ጥሩ ተወዳዳሪ የሚሆንበት ዕድል የተመናመነ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ምርት ላይ እሴት በመጨመር አነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎች እንዲሠሩ እና አርሶ አደሩ ወደ አግሮ ኢንዱስትሪ እንዲገባ የብድር አቅርቦት ወሳኝነት እንዳለው አመልክተው፤ እያረሰ የሚኖረውን አርሶ አደር ቁጥር በመቀነስ ወደ ኢንዱስትሪው ለማሸጋገር እና ለማንኛቸውም በግብርና ዘርፍ ላይ ሊመጡ ለሚገባቸው ለውጦች ትልቁ መፍትሔ ፋይናንስ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ከዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት (ፋኦ) ጋር ባደረገው ጥናት በኢትዮጵያ በሰብል ምርት ከ20 እስከ 30 በመቶ በአትክልትና ፍራፍሬ ደግሞ 51 በመቶ የምርት ብክነት እና መበላሸት መኖሩን ተገልጿል።

ብክነቱ በአጨዳ፣ በውቂያ፣ አርሶ አደሮች ወደ ቤት በሚያጓጉዙበት ወቅት እንዲሁም በእህል ጉድጓድ፣ በጎተራ ሲከማች መሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የግብርና ምርት ብልሽት ደግሞ በዋናነት ከማከማቻ መዋቅር አለመኖር ጋር የተያያዘ መሆኑንም መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

# በአምስት ዓመታት ለሁሉም መምህራን ሥልጠና በመስጠት ሰርቲፋይድ ለማድረግ እየተሠራ ነው

## - 5 ሺህ የትምህርት አመራሮች ሥልጠና ወስደው ሰርቲፋይድ ሆነዋል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በአምስት ዓመታት ውስጥ ለሁሉም መምህራን የሥራ ላይ ሥልጠና በመስጠት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ (ሰርቲፋይድ ) ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስታወቀ፡፡ ከዚህ በፊት በተሰጡ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ 5 ሺህ የትምህርት አመራሮች ሥልጠናቸውን አጠናቀው ሰርቲፋይድ መሆናቸውንም ገልጿል፡፡

በሚኒስቴሩ የመምህራንና ትምህርት አመራሮች ልማት ሥራ አስፈጻሚ ሙሉቀን ንጋቱ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በመላው ሀገሪቱ ለሚገኙ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት ዓይነት የትምህርት ደረጃ ላይ ብቁ ሆነው እንዲገኙ የሚያስችል የሥራ ላይ ሥልጠና በመስጠት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ (ሰርቲፋይድ) ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡

በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች መምህራን ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን የሚያሳይ ነው ያሉት ዶክተር ሙሉቀን፤ የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቀው አለማወቅ፣ የማስተማር ዘዴ እውቀት ማነስ፣ ዘመኑ የሚፈልገውን ቴክኖሎጂ ለመማር ማስተማር ሂደቱ በመጠቀም በኩል ያሉ ጉድለቶች በመምህራን ዘንድ በብዛት የሚስተዋሉ እጥረቶች ናቸው፡፡ ከብቃትም ባለፈ ለተማሪዎቻቸው ተገቢውን እውቀት ለማስጨበጥ ያላቸው ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት አሳሳቢ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ያልወሰዱ መምህራንንና አመራሮች የሥራ ላይ ሥልጠና ሲሰጥ መቆየቱን ጠቅሰው፤ በዚህም አምስት ሺህ የሚሆኑ የትምህርት አመራሮች ሠልጥነው ሰርቲፋይድ እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ነገር ግን በሀገሪቱ ካለው ሰፊ ፍላጎት አንጻር አሁንም ብዙ ሥራ ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡

በክረምት መርሃግብር የመምህራንን የትምህርት ደረጃ ለመሻሻል ሲሠራ እንደነበር አስታውሰው፤ በጥቂት ሳምንታት ሥልጠና ዲፕሎማ፣ ዲግሪና ሁለተኛ ዲግሪ መስጠት የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆልን ከማባባስ ያለፈ ውጤት እንዳልተገኘበት ተገምግሟል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚያስተምሩትን የትምህርት ዓይነትና ደረጃ በሚመጥን መልኩ ሥራውን እንዲያውቁትና ራሳቸውን ከጊዜው ጋር አብቅተው እንዲሄዱ የሚያደርግ የክረምት የሥራ ላይ ሥልጠና ይሰጣል ነው ያሉት፡፡

ሥልጠናው ከተቻለ በተያዘው ዓመት ካልሆነም ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ በስፋት እንደሚሰጥ ጠቅሰው፤ በአምስት ዓመታት ውስጥ ሁሉንም መምህራን አሠልጥኖ ለማጠናቀቅ መታቀዱን አመልክተዋል፡፡

ከሥልጠናው በኋላም ሥልጠናውን ማጠናቃቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት እንጂ የዲግሪ ወይም የሌላ ትምህርት ደረጃ ማስረጃ አይሰጥም ያሉት ሙሉቀን ንጋቱ (ዶ/ር) ፤ ሥልጠናውን ሲያጠናቅቁም ብሔራዊ ፈተና በማዘጋጀት የመምህራንን አቅም ለመፈተሸ እየተሠራ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

መምህራን የትምህርት ደረጃቸውን በምን መልኩ ያሻሽሉ ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት በሚኒስቴሩ እየተሠራበት መሆኑንም ዶክተር ሙሉቀን ተናግረዋል፡፡



ሙሉቀን ንጋቱ(ዶ/ር)

የትኛውም የትምህርት ሥርዓት ብቁና ጠንካራ መምህራን ከሌለው ውጤታማ ሊሆን አይችልም ያሉት ዶክተር ሙሉቀን፤ የመምህራን የትምህርት አመራሮችን ሚና በቴክኖሎጂ ማገዝ ካልሆነ በስተቀር በምንም ልንተካው አንችልም፡፡ በመሆኑም የምናስበውን ዓይነት የትምህርት ጥራት ለማምጣት መምህራንና ትምህርት አመራሮችን አቅም ለማጎልበት መረባረብ ያስፈልጋል፡፡

በኢትዮጵያ 700 ሺህ የሚደርሱ መምህራን እንዳሉ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡




# በኮምቦልቻ ከተማ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ሊገነባ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በኮምቦልቻ ከተማ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ለማስገንባት የአዲስ አበባ ባለሀብቶችንና ተቋማትን በማስተባበር የመሠረት ድንጋይ አስቀምጠዋል።

ከንቲባዋ ትናንት በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው እንዳስታወቁት፤ ከሥልጠናው በኋላ የለውጡ ትሩፋት የሆነውን የሰው ተኮር ሥራ ልምዳችንን ለማካፈልና ወንድማማች፣ እህትማማችነትን ለማጠናከር በኮምቦልቻ ከተማ የተስፋ ብርሃን የምገባ ማዕከል ለማስገንባት የአዲስ አበባ ባለሀብቶችንና ተቋማትን በማስተባበር የመሠረት ድንጋይ አስቀመጥናል ብለዋል።

በተጨማሪም በኮምቦልቻ ከተማ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎችን ጎብኝተናል ያሉት ከንቲባዋ፤ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪን የሚቆጥቡ ተኪና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ምርቶችን በጥራት የሚያመርቱ ፋብሪካዎች እየተበራከቱ እና አቅማቸውን እያሳደጉ መሆኑን ተመልክተናል ብለዋል።

የጀመርነው የብልፅግና ጉዞ በሁላችንም ትጋት እንዲሳካ በትብብርና በጋራ መሥራታችንን አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉም ገልጸዋል።

የሥልጠናው ተሳታፊዎች ሥልጠናው የአመራራችንን አቅም ከመገንባት ባሻገር ይበልጥ እንዲቀራረቡና እንዲተዋወቁ ዕድል እንደሚያመቻችላቸው እንዲሁም የአስተሳሰብና የተግባር አንድነትን እንደሚያጠናክርላቸው በውይይት ወቅት አንስተዋል።

በወሎ ኮምቦልቻ ከተማ ከሁሉም የሀገራችን ክልሎች የመጡ የመንግሥት አመራሮችን የማስፈፀም አቅም ለመገንባት በሚሰጠው ሥልጠና ላይ ተገኝቼያለሁ። ወሎ የፍቅር ሀገር ላደረገልን አቀባበል እናመሰግናለንም ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ትኩረት ለፍትህ ስርዓቱ

ፍርድ ቤቶች ሕግን የመተርጎም ሕገመንግስታዊ ተልዕኮ የተሰጣቸው አካላት ናቸው፡፡ ከሕግ ውጪ ተፈጽመዋል ለሚባሉ ድርጊቶችም ሕግንና ማስረጃን መሰረት በማድረግ በነጻነትና በገለልተኝት ፍትህ/ዳኝነት ይሰጣሉ፡፡ የዜጎችን የፍትህ ጥማት ያረካሉ፡፡ ዜጎች በሕግ ስርአቱ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያጎለብቱም ሌት ተቀን ይሰራሉ፡፡

እንደ አጠቃላይም ሕዝብ በፍትህ አካላት ላይ የጠነከረ እምነት ሲይዝ የሕግ የበላይነት ይረጋገጣል። በውጤቱም የሀገርና የሕዝብ ደህንነት ዋስትና ያገኛል፡፡ ሰላም ይሰፍናል፤ ፍትህ ይነግሳል፡፡ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ሕዝቡንም ፍትሃዊ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ይኖራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ከፍተኛ የፍትህ ፍላጎት አለ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛውን ጊዜ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ በመሬት፣ በተለያዩ ወንጀሎች፣ ከጎረቤት ጋር በሚኖሩ ያለመግባባቶች፣ ከቤተሰብ እና ከቤት ውስጥ ጥቃት ጋር በተያያዙ ችግሮች፣ ከገንዘብ ጋር በተያያዙ አለመግባባቶች እና ከሥራ ጋር በተያያዙ የሕግ ጉዳዮች ያጋጥሙታል። ሆኖም እነዚህን ችግሮች በሕግ አግባብ ለመፍታት የሚሄድበት መንገድ አታካች ከመሆኑም በላይ በሕግ አግባብ እልባት የሚያገኙት ጥቂቱ ብቻ ናቸው፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩትም በየዓመቱ 7 ነጥብ 4 ሚሊዮን ሰዎች የሕግ ጉዳይ አጋጥሟቸው ወደ ፍርድ ቤቶች ቢሄዱም ከእነዚህ ውስጥ መፍትሄ የሚያገኙት ከ30 በመቶ በታች ናቸው፡፡ 70 በመቶ የሚሆኑት በወቅቱ ሕጋዊ መፍትሄ ካለማግኘታቸውም በላይ በሚኖራቸው ምልልስ የጊዜና የኢኮኖሚ ኪሳራ ያጋጥማቸዋል፡፡ በየዓመቱ የሚተላለፉ መዝገቦች መብዛት አንድን ጉዳይ እልባት ለመስጠት የሚወስደውን ጊዜ የተራዘመ በመሆኑ የዜጎችን ፍትህ በጊዜው የማግኘት መብትን የሚጥስ ጉዳይ ሆኗል፡፡

የዘገየ ፍትህ እንደተነፈገ ይቆጠራል እንደሚባለው የሕግ ጉዳይ አጋጥሞት ወደ ፍርድ ቤቶች የሄደ ሰው ጉዳዩ እስኪፈጸምለት በርካታ ዓመታት ይቆጠራሉ፡፡ በዚህም ሕዝብ በፍትህ ስርዓቱ ላይ እምነት እንዲያጣ አድርጓል፡፡ እንደ አጠቃላይም ፍትህ ለዲሞክራሲ ግንባታ፣ ለሰላም እና ለልማት ሊወጣ የሚገባውን ሚና እንዳይወጣ አድርጎታል፡፡

ፍርድ ቤቶች ለዘመናት የተከማቹ ችግሮች ያሉባቸው የፍትህ ተቋማት ናቸው፡፡ መጓተት፣ የጥራት አለመኖርና ውስን ተደራሽነት የፍርድ ቤቶቻችን መለያ ከሆኑ ቆይተዋል፡፡ በሙስና፤ በምልጃ እና በትውውቅ ጉዳይን ማስፈጸምም በፍርድ ቤቶች አካባቢ ስለመኖሩም ብዙዎች ሲናገሩ ይሰማል፡፡

በሌላም በኩል የባለሙያዎች የአቅም ክፍተት፤ ብቁ ባለሙያዎችን ወደ ፍትህ ስርአቱ ለመሳብና ለማቆየት አለመቻል፤ የምርምርና የማሰልጠን አቅም ያለመዳበር፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ሌሎች መሰረተ ልማቶች አለማሟላት የፍትህ ስርዓቱ ማነቆዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም በስነምግባርም ሆነ በአቅም ግንባታ ረገድ የሚታዩ ክፍቶችን መሙላትና እንደ አጠቃላይ ለፍትህ ስርዓቱ በቂ ትኩረት መስጠት የጊዜው ጥያቄ ሊሆን ይገባል፡፡

በፍርድ ቤቶች የሚስተዋሉ የስነ-ምግባር ችግሮችን ያለ ርህራሄ ማስወገድ ወይም መታገል ያስፈልጋል። በዳኞችም ይሁን በድጋፍ ሰጪ ሠራተኞቻችን አካባቢ በሚስተዋሉ እና እያደጉ የመጡ የስነ-ምግባር ችግሮች በጊዜ ካልተቀረፉ የፍርድ ቤቶች ፍትህ/ዳኝነት የመስጠት የሞራል ልዕልና ሊኖረው አይችልም፡፡

በማኅበረሰብ ደረጃ ሰፊ የፍትህ ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ እና አስፈሊጊ በሚሆንበት ጊዜም መደበኛ የፍትሕ አሰጣጥ ዘዴዎችን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ በኢ-መደበኛ እና በመደበኛ ፍትሕ መካከል ድልድዮች መዘርጋት እና ዜጎች ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ጎን ለጎን በየአካባቢቸው በባሕላዊ መንገዶች ፍትህ እንዲያገኙ ማድረግን እንደ አንድ አማራጭ አድርጎ መውሰድ ይገባል፡፡

ሥር ነቀል የፍትሕ ለውጥ ሂደትን በኢ-መደበኛ እንዱሁም በመደበኛ፣ በክልል እንዲሁም በፌዴራል ደረጃዎች ማስጀመር እና የፍትህ ስርዓቱን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማገዝና ሰዎች ያለብዙ ውጣ ውረድ የሕግ ጉዳዮቻቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግ የፍትህ ስርዓቱ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የዳኝነት አገልግሎቱን ነጻነትና ተጠያቂነት የሚያጠናክሩ፤ ጥራትን የሚያሻሽሉ እና ተደራሽነትን የሚያጎለብቱ ሥራዎችን በማከናወን በፍትህ ስርዓቱ ላይ ሕዝቡ እምነቱን እንዲጨምር ማድረግ ያሻል፡፡

በአጠቃላይ የዜጎች በተቀላጠፈ ሁኔታ ፍትህ የማግኘት መብት በምንም ምክንያት ሊሸፋፈን የማይገባው ከመሆኑም በላይ እንደ ሀገር የዴሞክራሲና የልማት ጉዳይ ስለሆነ መንግስት የፍትህ ስርዓቱ ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጥ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሰው ሰራሽ አስተውሎት፤

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)

የሰው ሰራሽ አስተውሎት/Artificial Intelligence /AI/ጉዳይ ከሳይንስ አልፎ የማሕበራዊ፣ የኢኮኖሚ፣ የደህንነት፣ የሳይበር ጦርነት፣ የወታደራዊ ዝማኔ፣ የሉዓላዊነትና የልዕለ ኃያልነት እርካብ መቆናጠጫ ከመሆን አልፎ የጂኦፖለቲካ ሚዛን መለካኪያ ከሆነ ውሎ አደረ። በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት በAI የበላይ የሆነ ዓለምን በመዳፍ ለመጨበጥ ተጨማሪ አቅም ያገኛል። አሜሪካና ቻይና በዚህ ዘርፍ ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቁ ያሉት ለዚህ ነው።

ማን አሸናፊ ሆኖ እንደሚመጣ በቅርብ እናያለን። የAIን ጉዳይ በቁንጽል ሳይሆን በማዕቀፍ ማየት ያስፈልጋል። እንደ ሀገር የሚሰጠው ትኩረትም ይሄን ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል። የምዕራባውያን የስለላ፣ የደህንነትና የአለማቀፍ ግንኙነት ልሳን የሆነውና ተነባቢው የ"Foreign Affairs"መጽሔት ሰሞነኛ ዕትም በአንድ ጊዜ ከአንድም ሁለት ጥልቅ መጣጥፎችንና ትንተናዎቹን በAI ላይ ማድረጉ ምን ያህል ገዥ አጀንዳ እየሆነ እንደመጣ ያረጋግጣል።

ጀምስ ማኒካና ማይክል ስፔንስ በገራ፤ "The Coming AI Economic Revolution"በሚል ርዕስ ባስነበቡን መጣጥፍ፤ የAI አንድ ዘርፍ የሆነው አዲሱ ሰውሰራሽ አስተውሎት ወይም ጄነሬቲቭ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ብቻ ለዓለም ኢኮኖሚ በዓመት 4 ትሪሊየን ዶላር ያበረክታል። በዓለማችን በግዙፍነቱ 4ኛ እንደሆነ የሚነገርለት የጀርመን ጥቅል ኢኮኖሚ 4 ትሪሊየን ዶላር መሆኑን እዚህ ላይ ልብ ይሏል።

እንግዲህ ይህ ሌሎች እንደ አውቶሜሽን ያሉ የAI ዘርፎች ለኢኮኖሚው ከሚያመነጩት 11 ትሪሊየን ዶላር በተጨማሪ መሆኑ ነው። በAI ባቡር መነሻንና መዳረሻን ጠንቅቆ አውቆ በጊዜ መሳፈር ወሳኝ ስለሆነ ነው ትኩረት ተሰጥቶ የምናየው። ኢትዮጵያ አበክራ ከሶስት ዓመታት በፊት የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት አቋቁማ የሰው ሰራሽ አስተውሎትን በተለያዩ ተቋማት ስራ ላይ ለማዋል እየጣረች ያለችው ለዚህ ነው።

ሰው ሰራሽ አስተውሎትን በሀገር በቀል ተቋም ገርቶ በማሰልጠን ለሀገር ጥቅምና ልማት ማዋል ይገባል ሲሉ የቴክኖሎጂ ጉዳዮች አማካሪና በebs የቴሌቪዥን መርሀ ግብር አዘጋጅ ሰለሞን ካሳ፤ በኢትዮጵያ የሰው ሰራሽ አስተውሎት የሚገኝበት ደረጃና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ፤ የሰው ሰራሽ አስተውሎት በእርሻ፣ በአስተዳደር፣ በትምህርትና በሌሎች በርካታ አገልግሎቶች ላይ እንደሚተገበር፤ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ለኢትዮጵያ ክፍተትን በመሙላት፣ ወደኋላ ያስቀረን እና ያልተቀላጠፈ ስርዓታችንን ለማዘመን ያግዛል ሲሉም ተናግረዋል።

በተጨማሪም ኢትዮጵያውያን በዚህ ሂደት አልፈው ከሀገራቸው አልፈው ለዓለም ብዙ ማበርከት እንደሚችሉ፤ የሰው ሰራሽ አስተውሎት በዓለም ላይ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ብዙ ዘርፎች እንዲወለዱ ምክንያት መሆኑን፤ ዘርፉን እንደ ኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ባለ ሀገር በቀል ተቋም ገርቶ በራስ ልክ ማሰልጠንና ለበጎ ተግባር ማለትም ለሀገር ጥቅምና ልማት ማዋል ግድ እንደሚልም አሳስበዋል።

የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ከእድሜ አንጻር ገና ቢሆንም እየተንቀሳቀሰ ያለው ግን ከዚያ በላይ እንደሆነ፤ ኢትዮጵያን በአፍሪካ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ግንባር ቀደም የሚያደርጋትን ተቋም እውን ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ደግሞ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ኢ/ር) አክለው መግለጻቸው በመግቢያዬ ላጋራኋችሁም ሆነ በማስከተል ለማካፍላችሁ ታሪካዊ ዳራ መነሻ ሆኖኛል፡፡

በነገራችን ላይ መጭው ዘመን የ"AI"ነው። ባጠረ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የእያንዳንዳችን የሕይወት ቅንጣት የሚነካ ስለሆነ ስለ AI ግንዛቤ መያዝም ስላለበት ወይም AI Literacy መኀልበት ስለሚገባው ብዙኃን መገናኛዎች ብዙ ስራ ይጠብቃቸዋል።

የኢንዱስትሪ አብዮት በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ተጀምሮ በ19ኛው መክዘ ተጠናክሮ የቀጠለ ወሳኝ የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ እምርታ ነው ። አዳዲስ ፋብሪካዎች የተፈጠሩበት፣ የእንፋሎት ኃይል በስፋት ጥቅም ላይ የዋለበት፣ ማሽኖች ወደ ስራ የገቡበት፣ ምርትና ምርታመነት የጨመረበት እና ከተሞች የተስፋፉበትና ዛሬ የምንገኝበት ዓለም የተበየነበት ታላቅ ክስተት ነው። በሰው ልጆች ታሪክ ሶስት የኢንዱስትሪ አብዮቶች የተካሄዱ ሲሆን አራተኛውን ደግሞ ተያይዘነዋል።

ሁሉም የየራሳቸውን አዳዲስ የፈጠራና ኢኮኖሚያዊ ማዕበል አስነስተዋል። የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት ችቦ በእንግሊዝ ተለኩሶ ወደ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ የተቀጣጠለ ሲሆን የዘመነ ፋብሪካና የእንፋሎት ኃይል መለያው ናቸው። ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት በ19ኛው መክዘ መገባደጃ ተጀምሮ እስከ 20ኛው መክዘ መጀመሪያ የቀጠለ ሲሆን እንደ መኪናና አውሮፕላን ያሉ መጓጓዣዎች፤ የኤሌክትሪክ ኃይልና የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች በስፋት ጥቅም ላይ የዋሉበት ነው።

ሶስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ከ20ኛው መክዘ አጋማሽ ዛሬ ድረስ የቀጠለው ሲሆን የዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ በይነ መረብ ወይም ኢንተርኔት፣ አውቶሜሽን፣ ሮቦቲክስና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች የተስፋፉበትና በስፋት ጥቅም ላይ

ወደ ገጽ 14 ዞሯል


**ስብዙዎቻችን የሰው ሰራሽ አስተውሎት አዲስ ግኝትና ቴክኖሎጂያዊ እመርታ የቅርብ ጊዜ ክስተት ቢመስለንም የዘርፉ ልሒቃን ግን ጥንስሱ ጥንታዊ ነው ሲሉ ሀተታ ተፈጥሮንና ስነ ቃልን በዋቢነት ያወሳሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተስፋም ስጋትም ይዞ ወደፊት እየመጣ ያለው ሰው ሰራሽ አስተውሎት ግን የተጀመረው በ20ኛው መክዘ አጋማሽ ሲሆን የኮምፒውተር ሲቃውንት ስልተ ቀመር ወይም አልጎሪዝምና አስበው የሚሰሩ ማሽኖች ወደ ስራ እየገቡበት ያለ ጊዜ ነው**

# 163 የፌዴራል ተቋማት በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት ግዥ እያከናወኑ ነው

## - ከ38 ሺ በላይ የንግዱ ማህበረሰብ ሥርዓቱን ተቀላቅለዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- 163 የፌዴራል ተቋማት ግዥያቸውን በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት እያከናወኑ መሆኑን የግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡ ከ38ሺ በላይ የንግዱ ማህበረሰብ አባላትም በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት እየተጠቀሙ መሆኑ ተጠቁሟል፡፡



**አቶ ሀጂ ኢብሳ**

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀጂ ኢብሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣ በ2016 በጀት ዓመት ከተጠሪዎቻቸው ውጪ 169 የሚሆኑ የፌዴራል ተቋማት ሙሉ ለሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት እንዲገቡ የሚደረግ ሲሆን፣ እስካሁን 163 የፌዴራል ተቋማት በግዥ ሥርዓቱ ውስጥ ገብተዋል፡፡ የቀሩት ስድስት የሚሆኑ ተቋማት ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ አራቱ በትግራይ የሚገኙ ዩኒቨርሰቲዎች ሲሆኑ ሁለቱ በአማራ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው፡፡

በትግራይ ክልል የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ተፈጠሮ በነበረው ግጭት በዩኒቨርሲቲዎቹ ያለው መሠረተ ልማት ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ የግዥ ሥርዓቱን በወቅቱ ለማስጀመር ያልተቻለ ሲሆን በአማራ ክልል የሚገኙት እንጅባራ እና ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲዎች ወደሥርዓቱ ለመግባት በሂደት ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ በአሁኑ ወቅት መሠረተ ልማቱ እየተሠራ ሲሆን ሥራውን ለማቀላጠፍ ያስችል ዘንድ ለባለሙያዎች ሥልጠና እየተሰጠ ሲሆን ከሁለት ወር በኋላ ወደ ግዥ ሥርዓቱ የሚገቡበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት ከ169 የፌዴራል ተቋማት 74 የሚሆኑት በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓቱ ግዢ የፈጸሙ ሲሆን 100 የሚሆኑት ደግሞ በማንዋል ግዥ መፈፀማቸውን አቶ ሀጂ ጠቁመዋል፡፡

በወቅቱ ነጋዴው ሁለት ቦታ ላይ የመቆም፣ ፌዴራል ተቋማትም አንዱ በኤሌክትሮኒክስ ግዥ እፈፅማለሁ፣ ሌላው በማንዋል እንድገዛ ይፈቀድልኝ የሚል ጥያቄ የማንሳት አዝማሚያዎች እንደነበሩ የጠቀሱት አቶ ሀጂ፣ ይህም ወጥ የሆነ የግዥ ሥርዓት ባለመኖሩ የተነሳ ነው ብለዋል፡፡

የንግዱ ማህበረሰብም ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክስ ግዥ ሥርዓት ውስጥ አለመግባት፣ የኤሌክትሮኒክስ ግዥ እስኪለማመድ በማንዋል የመግዛትና የመሸጥ ፍላጎቶች እንደነበሩ እና በዚህም ትልቁ ተግዳሮት የነበረው በኤሌክትሮኒክስ ግዥ የሚፈጽሙና በማንዋል ግዥ የሚፈጽሙ የፌዴራል ተቋማት መኖራቸው ከፍተኛ ማነቆ እንደነበር አቶ ሀጂ አስታውሰዋል፡፡

አቶ ሀጂ፣ በአሁኑ ወቅት በትልልቅ ደረጃ ከሶስት እስከ 20 የተለያየ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ከ15ሺ በላይ የሆኑ ነጋዴዎች መመዝገባቸውን ጠቁመው፣ የእያንዳንዱ ፈቃድ ሲታይ ከ38ሺ በላይ የሚሆን የንግዱ ማህበረሰብ ተመዝግቧል ብለዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም ሀምሌ ወር አንድ መቶ የነበረው የንግዱ ማህበረሰብ ተሳትፎ አሁን ላይ ከ38ሺ በላይ መድረሱን አቶ ሀጂ ገልጸዋል፡፡

# ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ግሽበትን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለማግኘት ባንኩ የሠራውን በጥንካሬ አንስተዋል።

የሀገር ውስጥ ብድር በ 14 በመቶ ጣሪያ በመገደብ እና መንግሥት ለበጀት ጉድለት ከብሔራዊ ባንክ የሚወስደውን የብድር መጠን በመቀነስ የዋጋ ግሸበቱ እንዳይባባስ ለማድረግ የተወሰደውን ርምጃም በበጎነት አንስተዋል።

ቋሚ ኮሚቴው በተለያዩ መለኪያዎች መሠረት ባንኩ የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት በማስፈን ጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑን መገንዘቡንም ነው የጠቆሙት። ዓለም አቀፍና ሀገር አቀፍ ተጽእኖ ቢኖርም የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበትም አሳስበዋል።

የፋይናንስ ተደራሽነትን ለማስፋፋት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመፍታት ትኩረት መስጠት አለበት ያሉት ሰብሳቢው፣ የወርቅ ግዢ ካምናው የተሻለ ቢሆንም በዘርፉ የሰፈነውን ሕገ ወጥ ንግድ ለመቆጣጠር ሰፊ ሥራ መሠራት እንዳለበት ጠቁመዋል።

ምክትል ሰብሳቢው አብርሃም አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለመፍጠር፣ አገልግሎቱን ለማዳረስ፣ አካታችና ዲጂታላይዝ ለማድረግ የተወሰደው ውጤታማ ሥራ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባው ጠቁመዋል።

ሕገ ወጥ የውጭ ምንዛሬ ግብይትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት መሥራት እንደሚገባም ተናግረዋል።

የዋጋ ንረት የመቀነስ አዝማሚያ መታየቱን ያስታወሱት ዶክተር አብርሃም፣ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ወደ 20 ነጥብ ሶስት ለማውረድ ባንኩ የራሱን ሚና በመጫወት ቀድሞ ለማሳካት ጠንካራ ሥራ መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል።

የባንኩ ገዢ አቶ ማሞ ምህረቱ ባቀረቡት ሪፖርት፣ በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ በኢትዮጵያ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲኖር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

አበዳሪ ሀገራት በዕዳ ክምችትና በዓለም አቀፍ ተጽእኖ ብድርና ርዳታ መቀነሳቸውን በመጠቆምም፣ ባለፈው ዓመት ግን ከተለያዩ ገቢዎች 24 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ተናግረዋል።

አራት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለነዳጅ ክፍያ፣ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ደግሞ ለማዳበሪያ ግዢ ወጪ መደረጉን አንስተው፣ የዋጋ ንረቱ የቆየ ችግር ቢሆንም በአንጻሩ እየቀነሰ መሆኑን አመልክተዋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ከ30 በመቶ በላይ የነበረው የዋጋ ንረት በተወሰዱ የማሻሻያ ርምጃዎች እንዲቀንስ መደረጉን በመጠቆምም፣ በመስከረም ወር 2016 ዓ.ም ወደ 27 ነጥብ ሰባት በመቶ ሰኔ መጨረሻ ደግሞ ወደ 20 በመቶ ለማድረስ ይሠራል ብለዋል።

ባንኮች የሚሰጡት ብድር እንዲገደብ መደረጉና ለመንግሥት የሚሰጠው ብድር እንዲቀነስ መወሰኑ ለውጤቱ መገኘት አስተዋጽኦ ማድረጋቸውን ጠቅሰዋል።

የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ አምራች ዘርፎችን በማበረታታት፣ ሬሚታንስን በማሳደግና የሀገር ውስጥ ተኪ ምርቶችን በማበረታታት ትኩረት እንደሚደረግም ነው የተናገሩት።

በ2010 ዓ.ም አራት ሺህ 842 የነበሩት የባንኮች ቅርንጫፍ ብዛት መስከረም 2016 ዓ.ም 11 ሺህ 861 መድረሳቸውን፣ ዜሮ ነጥብ 73 የነበረው ተቀማጭ ገንዘብ በሶስት እጥፍ አድጎ ሁለት ነጥብ ሶስት ትሪሊዮን መድረሱንም አመልክተዋል።

በፋይናንስ አመላካቾች በተደረገ ግምገማ የተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት በማስፈን የኢትዮጵያ ባንኮች ጤናማ፣ ትርፋማና የተረጋጉ መሆናቸው መለየቱን አንስተዋል። የክፍያ ሥርዓት በአመዛኙ ወደ ዲጂታል እየተለወጠ መሆኑንና እአአ 2023 አራት ነጥብ 776 ትሪሊዮን ብር በዲጂታል መከናወኑንም አቶ ማሞ ተናግረዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፣ አንጻራዊ ነጻነቱን ጠብቆ ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያግዘው የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ እየተከለሰ ነው። የኢትዮጵያ የፋይናንስ አካዳሚ የማደራጀት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶታል።

ለውጭ ባንኮች የባንክ ሥራ ፈቃድ የሚፈቅደው፣ የባንክ ቢዝነስ ሥራ ማሻሻያ አዋጅ፣ የውስጥ ቁጥጥርና የአደጋ አስተዳደር መመሪያ፣ ከሸሪአ ሕግ ጋር የተጣጣመ የፋይናንስ ፖሊሲና መመሪያ እንዲሁም የባንክ አገልግሎት ለአካል ጉዳተኞች ምቹና ተስማሚ እንዲሆን የሚያስችሉ መመሪያዎች እየተዘጋጁ መሆናቸውን አቶ ማሞ አብራርተዋል።

የተረጋጋ የዋጋና የውጭ ምንዛሬ እንዲኖር፣ የተረጋጋ ፋይናንስ እንዲሰፍን፣ የፋይናንስ አካታችነት፣ የአሠራር፣ የሰው ሃይል የቴክኖሎጂ ልህቀት እንዲመጣ የመልካም አስተዳደር ሥርዓት እንዲሰፍን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑንም ነው የገለጹት።

# መንግሥት ለአፈር ማዳበሪያ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ገበያን ለማረጋጋት ከፍተኛ ድጎማ አድርጓል። በ2014/ 15 ምርት ዘመን 15 ቢሊዮን ብር፣ በ2015/16 ምርት ዘመን 21 ቢሊዮን ብር እንዲሁም በ2016/17 ምርት ዘመን 16 ቢሊዮን ብር፣ በድምሩ ለሦስት ተከታታይ ዓመታት የ52 ቢሊዮን ብር ድጎማ አድርጓል።

ለ12016/17 ምርት ዘመን የሚውል 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ እንደሚገዛ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ እስካሁን የ 14 ነጥብ 79 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ መፈጸሙን አስታውቀዋል።

ከ19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል ውስጥ ስምንት ነጥብ ሁለት ኩንታል የዩሪያ አፈር ማዳበሪያ መሆኑንና ቀሪው 11 ነጥብ 19 ሚሊዮን ኩንታል ኤን. ፒ. ኤስ መሆኑን ጠቅሰዋል። ይህ ባለፈው ዓመት ከተገዛው 12 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ኩንታል አንጻር ከፍተኛ ጭማሪ እንዳለውም ገልጸዋል።

እስካሁን የ 11 ነጥብ 19 ሚሊዮን ኩንታል ኤን. ፒ. ኤስ. ዝርያ እና ሦስት ነጥብ 56 ሚሊዮን ኩንታል ዩሪያ ማዳበሪያ ፤ በድምሩ የ 14 ነጥብ 79 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ መፈጸሙን ነው ያስታወቁት። ኢትዮጵያ በታሪኳ ከፍተኛ የሆነ የማዳበሪያ ግዥ የፈጸመችው በዚህ የምርት ዘመን መሆኑንም ጠቁመዋል።

ባለፈው ዓመት የመጀመሪያዋ መርከብ ታህሳስ 18/2015 ዓ.ም መድረሷን ያስታወሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ በዚህ ዓመት 51 ሺህ 420 ሜትሪክ ቶን ዩሪያ የጫነች የመጀመሪያዋ መርከብ ጥቅምት ወር ላይ ጅቡቲ ወደብ ላይ መድረሷንና ይህም በማዳበሪያ አቅርቦት ታሪክ የመጀመሪያው እንደሆነ ተናግረዋል።

ለ2016/17 የምርት ዘመን እስከ ህዳር 19 ቀን 2016 ዓ.ም 207 ሺህ 295 ሜትሪክ ቶን የዩሪያ ማዳበሪያ ጅቡቲ ወደብ መድረሱንና ከዚህ ውስጥም 104 ሺህ 304 ሜትሪክ ቶን ዩሪያ ወደ ሀገር ውስጥ መጓጓዙን ሚኒስትር ዴኤታዋ ገልጸዋል።

በተመሳሳይ ከህዳር 21 እስከ ታህሳስ 4 ቀን 2016 ዓ.ም 174 ሺህ 500 ሜትሪክ ቶን ኤን.ፒ.ኤስ ቦሮን የጫኑ ሶስት መርከቦች ወደ ጅቡቲ እንደሚደርሱ ገልጸዋል።

ቀድሞ የነበረውን የግዢ መመሪያ መቀየር፣ የግብርና ሥራዎች ኮርፖሬሽን ቦርድ በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ማድረግ እና የቴክኒክ ኮሚቴ እንዲቋቋም ማድረግ፣ የተለያዩ የግዢ አማራጮችን በመጠቀም ግዥ ማከናወንን ጨምሮ በርካታ ተግባራት በሚኒስቴሩ እንደተፈጸሙም አስታውቀዋል።

# በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ወገኖች ርዳታ ተሰራጭቷል ብለዋል።

ከዚህ ውስጥ 3 ነጥብ 6 ሚሊዮን ዜጎች የገንዘብ ርዳታ የተደረገላቸው ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ምግብ ነክ ድጋፎች እንደተደረገላቸው አቶ አታለለ ጠቁመው፣ ርዳታው በገንዘብ ሲተመን 7 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ አታለለ እንዳሉት፣ በሁለተኛው ዙር ርዳታ 610 ሺህ ኩንታል እህል እንዲከፋፈል ተደርጓል። እንዲሁም 54 ሺህ ኩንታል አልሚ ምግብና አንድ ሚሊዮን ሊትር ዘይት ለእናቶች ለህጻናትና ለነፍሰጡር የማዳረስ ሥራ ተሠርቷል። ከዓለም ባንክ በተገኘ ርዳታም 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች እንዲከፋፈል ተደርጓል።

እንደ አቶ አታለለ ማብራሪያ፣ ከላይ የተጠቀሰው ቁጥር በጎርፍ ምክንያት በሶማሊያ ክልልና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ የተፈናቀሉ ወገኖችን አያካትትም።

ከሰሞኑ በሶማሊያ ክልል በተከሰተው ጎርፍ መንግሥት አንድ ሺህ 821 ኩንታል የስንዴ ዱቄትና ሩዝ ተልኳል ያሉት አቶ አታለለ፣ 9 ሺህ 200 ኪት ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችም ድጋፍ መደረጉንም ጨምረው ገልጸዋል።

ከመከላከያ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ሄሊኮፕተር በመጠቀም የሰዎችን ሕይወት የማዳን፣ የምግብ ቁሳቁሶችን፣ መድሃኒት፣ አጎበርና የውሃ ማጣሪያ ኬሚካል የማሰራጨት ሥራዎች መሠራታቸውን አቶ አታለለ ጠቁመው፣ ሌሎች ድጋፎች እየቀረቡ መሆናቸውንም ገልጸዋል። አሁን ባለው ሁኔታ በሶማሌ ክልል ችግር ለገጠማቸውን ዜጎች ድጋፍ ማድረግ መቻሉንም ተናግረዋል።

በተመሳሳይ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን ዳሰነች ወረዳ ባጋጠመ የጎርፍ አደጋ 16 ሺህ 648 አባ ወራዎችና እማ ወራዎች ከቀያቸው መፈናቀላቸውን ጠቁመው፣ ለነዚህ ዜጎች የሚሆን 3 ሺህ 140 ልዩ ልዩ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ተልከዋል ብለዋል።

በችግር ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ወደፊት ምን አይነት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል የሚለውን በመለየት አስፈላጊውን ድጋፍ ኮሚሽኑ እንደሚያደርግም የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አታለለ ገልጸዋል።

# ‹‹አመራሩ የሕዝቡን ርካታ ለማረጋገጥ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ማዕከል ተገኝተው የአመራሮችን የሥልጠና ሒደት በተመለከቱበት ወቅት እንዳሉት፣ ሠልጣኞች በሥልጠናው የሚያገኙትን ግብዓት ተግባራዊ በማድረግ የሕዝቡን ርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ መትጋት አለባቸው።

በተለይም በሰላም፣ በልማትና በመልካም አስተዳደር ሥራዎች ላይ ይበልጥ ውጤት ለማምጣት ሊተጉ ይገባል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ ፤ ሁለንተናዊ ብልጽግና የማረጋገጥ ጉዞን ለማፋጠን ሀገራዊ ራዕይን በአግባቡ መገንዘብና ለተግባራዊነቱ መረባረብ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በሌላ በኩል በክልሉ ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ከአመራሮች ጋር ውይይት ያደረጉት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ ባስተላለፉት መልእክት፣ በክልሉ በተፈጠረው ግጭትና አለመረጋጋት የተነሳ ከወትሮው በተለይ ሁኔታ ማከናወን ያለብንን የልማት ሥራ ለማከናወን እንቅፋት መሆኑን ጠቁመዋል።

በመከላከያ ሠራዊትና በክልሉ የፀጥታ ኃይል፣ አጠቃላይ አመራሩና ሰላም ወዳዱ ሕዝብ በቅንጅት በሠሩት ሥራ አብዛኛው የክልሉ አካባቢዎች ላይ አንፃራዊ ሰላም እንዲሰፍን መደረጉን ጠቅሰው፣ የክልሉን ሰላም ለማረጋገጥና ወደ ልማት ሥራዎቻችን ለመመለስ ባለን ጽኑ ፍላጎት በተከታታይ የግንዛቤ ማሳደግ ሥራዎችን መሥራታችን አሁን ለተገኘው አንጻራዊ ሰላም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ገልጸዋል።

የተገኘውን አንጻራዊ ሰላም ለማጽናት ወቅቱንና ሁኔታዎችን ያገናዘበ የጋራ አመራር የመስጠትና የማረጋገጥ ተግባር ከመላው አመራር እንደሚጠበቅ የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ ሕዝባችን ካለበት ችግር ውስጥ በፍጥነት ለማውጣት ከወትሮው የተለየ ሥራ ይጠይቃል ብለዋል።

ከሰሞኑ ከሕዝባችን ጋር ባደረግናቸው የውይይት መድረኮች ያገኘናቸውን እጅግ ገንቢ እና ተራማጅ ሃሳቦችን በተጨባጭ ወደ ተግባር በመቀየር የክልላችንን ለሰላም ፤ ለልማትና ለመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል። ድክመቶቻችንን ላለመድገም በአዲስ መታደስና ለትውልዱ ታሪክ መጻፍ ይገባናል ማለታቸውን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን መረጃ ያመለክታል።

# ወቅታዊ

# ‹‹ከፋይናንስ አቅርቦት ቀጥሎ የግብርናው ዘርፍ ትልቁ ችግር የእህል ማከማቻ መዋቅር አለመኖር ነው››

**ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር)**

**-የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር**

ምሕረት ሞገስ



የአርሶና አርብቶ አደሩን አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ ድጋፍ ከሚያደርጉ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት አንዱ ነው። ተቋሙ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት እንዲሁም የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ከሚሠራቸው ሥራዎች መካከል ለአርሶ እና አርብቶ አደሩ የሚሰጠው የምክር አገልግሎት አንደኛው ነው። ተቋሙ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ለአርሶ አደሩ የሚሰጠውን የምክር አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ቀላልና ምቹ ማድረግ የሚያስችለውን ‹‹8028›› የተባለ የስልክ ጥሪ አገልግሎት መስጫን ተግባራዊ አድርጓል።

አርሶና አርብቶ አደሩ በእጅ ስልኩ ወደ ‹‹8028›› እየደወለ በግብርና ሥራው እና ከግብርና ጋር ተያይዞ ለሚገጥመው ማንኛውም ችግር መፍትሔ እያገኘ መሆኑን የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት የሠጠው መረጃ ያመለክታል። ከእርሻ ጋር ተያይዞ በሰብል ምርት ሂደት ላይ ብቻ ሳይሆን በአሁን ወቅት ደግሞ የገበያ መረጃን ለማካተትና ለአርሶና አርብቶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችለውን ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ይፋ አድርጓል።

በተጨማሪ ከገበያው ባሻገር በሰብል ምርቶች ላይ ብቻ የነበረውን የምክር አገልግሎት በእንስሳት ሃብትም ለማስፋት እየሠራ እንደሚገኝ ይፋ አድርጓል። እስከ አሁን በተለይም በአፋርና በሶማሌ ክልሎች 130 ሺ የሚደርሱ አርብቶ አደሮች በዚህ መረጃ እየተጠቀሙ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል፡፤

ሌላው የኢትዮጵያ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት በግብርና ግብዓት አቅርቦት ላይ ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት ያስችላል የተባለለትን ዲጂታል የክፍያ ሥርዓት ሳይም ከክፍያ የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ተቋም ጋር በመተባበር በጋራ ለመሥራት ሰሞኑን ተፈራርሟል። በዚህ እና በሌሎችም በአጠቃላይ ተቋሙ በሚሠራቸው ሥራዎች ዙሪያ ከኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ማንደፍሮ ንጉሤ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ምን እየሠራ ነው ከሚለው እንጀምርና እንቀጥል?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ትልቁ ሥራችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል። አንደኛው የግብርና ዘርፉ ላይ ትላልቅ ማነቆ የሚባሉ እና ለረዥም ጊዜ አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮችን መለየት እና ለችግሮቹም የመፍትሔ ሃሳብ ማመንጨት ነው። ለዚህ ጥናት እና ምርምር የሚሠራ አንድ የሥራ ክፍል እና ቡድን አለ። በጥናት ክፍሉ የሚመጣው ምክረሃሳብ በቀጥታ በሚመለከታቸው አካላት እንዲተገበር ይሠራል። ተግባሪዎች የምንላቸው የግብርና ሚኒስቴር፣ በክልል፣ በዞን እና በወረዳ ደረጃ ያለ የግብርና ቢሮዎች በቀላሉ ሊተገብሩት የሚችሉት ከሆነ የጥናቱ ምክረ ሃሳብ እንዲተገበር ይደረጋል።

አንዳንዴ ምክረ ሃሳቡን ለመተግበር ተጨማሪ ዕውቀት እና ክህሎት የሚያስፈልግበት ጊዜ ያጋጥማል። በዛ ጊዜ የትግበራ ድጋፍ እንሠጣለን። እንዲተገበር አጋዥ ኃይል ማለትም ባለሙያዎችን እናስቀምጣለን። አፈር ላይ፣ ውሃ ላይ፣ የኅብረት ሥራዎች አሠራር ላይ ምርምር የሚያካሒዱ ብቻ ሳይሆኑ እንዲተገበር የሚያግዙ ባለሙያ እናስቀምጣለን። እነርሱ ምክረሃሳቡ እንዲተገበር አጋዥ ኃይል ይሆናሉ ማለት ነው። ባለሙያ በሚያስፈልግበት ቦታ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው እንዲተገበር ያደረጋሉ።

ስለዚህ ምክረ ሃሳቡን በመስጠት ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ባለሙያም አብሮ ሠርቶ አሳይቶ መረጃ ሰብስቦ ከዛ ወደ ትግበራ የሚገባበት ሁኔታ ይኖራል። በተጨማሪነት ግን ባለሙያ ገብቶበትም የማይተገበርበት ሁኔታ ያጋጥማል። በዚህ ጊዜ የሚመለከታቸው አካላት ይሳተፋሉ ማለት ነው። ለምሳሌ የግብርና ግብይት ሥርዓት ይኖራል። የአርሶ አደርን መሬት ኩታ ገጠም አድርጎ በመካናይዜሽን በትራክተር እንዲታረስ፣ በትራክተር እንዲዘራ፣ በኮምባይነር እንዲታጨድ ይፈለጋል።

አርሶ አደሮች ሰብስበው ለቤተሰብ ብቻ የሚበቃውን አስቀርተው፤ ቀሪውን ለገበያ እንዲያቀርቡ ማድረግ ላይ የሚሠራ ሲሆን፤ ሥራው ምርታቸውን ሲሸጡ የመደራደር አቅማቸውን ማሳደግንም ያካትታል። በዚህ ጊዜ ውጣ ውረድ ያለው ምርትም ሆነ ገበያ አይኖርም። ሁሉም የምርምር ውጤት ስለሚጠቀሙ ምርታማነታቸው ከፍተኛ ይሆናል። ይህ ደግሞ እንደሀገርም ምርታማነታችንን በከፍተኛ ደረጃ ይጨምረዋል።

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አርሶ አደሩ ምርታማነቱ ጨምሮ ከራሱ አልፎ ለገበያ አቅርቦ ኑሮውን እንዲያሻሽል ነው። ያ ማለት ኑሮ ሲሻሻል ከግብርና አልፎ ወደ ሌላ ኢንቨስትመንት ይገባል። በዛ ክላስተር የተደራጁ አርሶ አደሮች ወደ ፊት ወደ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ይቀየራሉ። እርሻው ላይ መቆየት የሚፈልግ ሰው እዛው እርሻው ላይ ይሠራል። የማይፈልግ ሰው ደግሞ በኩታ ገጠም አንድ ላይ ኢንተርፕራይዝ አቋቁሞ ቀጥሮ ሊያሠራ ይችላል። ይህንን በማድረግ ወደ መካናይዜሽን ሲሸጋገር፤ በርካታ ሰዎችን የያዘው የግብርናው ዘርፍ የሰው ኃይሉ ወደ ኢንዱስትሪ ይሸጋገራል። በዚህ ጊዜ ወደ ኢንዱስትሪ ሽግግር የምንለው ዕውን ይሆናል ማለት ነው። ይሔንን በምናደርግበት ጊዜ የግብርና ትራንስፎርሜሽንን እውን ስናደርግ አብዛኛው ሰው ካመረተው ውስጥ 75 በመቶ የሚሆነውን የሚሸጥ ከሆነ የግብርና ትራንስፎርሜሽን እውን ሆኗል ማለት ነው።

ከ75 በመቶ በታች ከሆነ ገበያው አላደገም ማለት ነው። ለገበያ የሚሔደው እየበዛ በሔደ ቁጥር ግን ወደ ኢንዱስትሪ እና ወደ አግሮ ፕሮሰሲንግ ለመሔድ ያስችላል። ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገውን ሽግግር ይፋጠናል ማለት ነው። ለምሳሌ አርሶ አደሮች ተደራጅተው የብቅል ገብስ እያመረቱ፤ የብቅል ገብስ ያቀርባሉ። አርሶ አደሮች ተደራጅተው አኩሪ አተር አምርተው ዘይት ለሚጨምቅ ኩባንያ ያቀርባሉ። አርሶ አደሮች ተደራጅተው አቮካዶ አምርተው ወደ ውጪ ለሚልክ ድርጅት ያቀርባሉ። አቮካዶ ተመርቶ ዘይት እና ጁስ እየተዘጋጀ ነው። ይህ እየቀጠለ ሲሔድ ግብርና ኢንዱስትሪውን እየመገበ ኢንዱስትሪው ይበልጥ እየተስፋፋ፤ ግብርና ላይ የሚኖረው የሰው ኃይል ደግሞ በመካናይዜሽን እየተተካ እየቀነሰ ወደ ኢንዱስትሪው መሔድ ይችላል። ስለዚህ ግብርናን እንደ ቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ እያዩ በክላስተር የተደራጁ አርሶ አደሮች ሕጋዊ ሰውነት እንዲኖራቸው መበደርም ማበደርም እንዲችሉ ሥራውን ማፋጠን የኛ ተግባር ነው።

ከመካናይዜሽን ክላስተር ወደ ኩታ ገጠም የግብርና ምርት ክላስተር ያሸጋገርናቸው አርሶ አደሮች አሉ፡፤ ከዚህ ደግሞ በቀጣዮቹ ሁለት እና ሦስት ዓመታት ወደ ኢንተርፕራይዝ የምናሸጋግራቸው አሉ። በዚህ የሽግግር ሒደት ውስጥ በርካታ ፕሮጀክቶች አሉ። አንደኛው ምርታማነትን ለመጨመር ወሳኙ ዘር ነው። ስለዚህ ዘር የሚያባዙ አርሶ አደሮችን በኅብረት ሥራ አደራጅተን ኅብረት ሥራን መሠረት ያደረገ ዘር እያመረቱ አሽገው ለሌሎች አርሶ አደሮች እየሸጡ ነው። ስለዚህ በልዩ ሁኔታ አጠቃላይ ምርት ከማምረት ወደ ዘር ማምረት የቀየርናቸው አርሶ አደሮች አሉ ማለት ነው።

የመካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪዎች አሉን። አሥር የመካናይዜሽን ማዕከላትን አቋቁመናል። እነዚህ የራሳቸው ትራክተር አላቸው፤ አርሶ አደሮች ትራክተር መግዛት አይጠበቅባቸውም። መከራየት፣ መጠቀም እና መክፈል ይችላሉ። ይህ አገልግሎት በመስጠቱ ግብርናው በጣም ይዘምናል። የሚባክን እህል አይኖርም። እንደአሁኑ ማለትም ዝናብ ሲያጋጥም በአንድ ቀን ውስጥ አጭዶ ወደ ማከማቻ ማስገባት ይችላል ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹የእናንተን ትራክተር አልፈልግም፤ ሠልጥኜ ኦፕሬተር መሆን እፈልጋለሁ።›› የሚሉ ወጣቶችም ካሉ፤ ማዕከሉ ያሰለጥናል፤ ብቁ ያደርጋቸዋል። ይህ በማዕከል የሚሠራ ሲሆን፤ አርሶ አደር በግሉ ገዝቶ አሠርቶ ሲበላሽበት ደግሞ ከተማ ውስጥ የጋራዥ አገልግሎት እንደሚሠጠው ሁሉ የጋራዥ አገልግሎት እና የመለዋወጫ አቅርቦት ሥራም ይሠራል። ማዕከላቱ ከውጪም አስመጥተው መለዋወጫ ያቀርባሉ። እነዚህን የመካናይዜሽን አገልግሎት የሚሠጡ ማዕከላት ሁለተኛ ፕሮጀክቶቻችን ናቸው።

ሦስተኛው የኢንስቲትዩቱ ሥራ ግብዓት ነው። አሁን መንግሥት እያመጣ መንግሥት እያሠራጨ ነው። በእኛ በኩል በየወረዳው 325 ሱቆችን አቋቁመናል። ሱቆች ግብዓቶችን ይገዛሉ፤ ለአርሶ አደሩ ይሸጣሉ። እነዚህ ሁሉን በአንድ የሚይዙ ሲሆን፤ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ የግብርና ኬሚካል እና የእንስሳት መድኃኒት እንዲሁም ሁሉም ነገር አላቸው። አርሶ አደሩ መድኃኒትን ያለአግባብ እንዳይጠቀም ማሠልጠኛ አላቸው። ስለዚህ አርሶ አደሩን የሚደግፉ 325 ሱቆች እና 10 የመካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት አሉን። በሞዴላችን 70 በመቶውን እኛ እንሸፍናለን። 30 በመቶ እነርሱ ይሸፍናሉ።

የመካናይዜሽኑን ሥራ ከዩኒየን ጋር አያይዘነዋል። ሱቆቹ ደግሞ የግለሰቦች ሲሆኑ፤ የሚያገኙት ተወዳድረው ነው። አራተኛው ፕሮጀክታችን ደግሞ የገበያ ክላስተሮቹ ዝናብን መሠረት ያደረጉ ናቸው። ስለዚህ የሚያመርቱት አንድ ጊዜ ነው። በእኛ በኩል ሁለት ጊዜ ማምረት እንዲችሉ የመስኖ አውታር መዘርጋት፤ በተለይም በፀሐይ ብርሃን (በሶላር) እንዲዘረጋ እየሠራን ነው። ይህም በእያንዳንዱ ግለሰብ በበርካቶች ቤት እየገባ ይገኛል። ይህ የኮሪያ ሞዴል ሲሆን፤ አሁን ከግለሰብ ቤት ወደ ማኅበረሰብ ደረጃ እያደገ ይገኛል።

ከፀሐይ ኃይል በተጨማሪ ውሃው ለመጠጥ፣ ለንጽሕና መጠበቂያ (ሳኒቴሽን) እና ለመስኖ እንዲሁም ለብዙ አገልግሎት ይሆናል። ከፀሐይ ብርሃን የሚገኘው ኃይል ውሃ እንዲገኝ የሚረዳ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በገጠር ለመብራት አገልግሎትም ይሆናል። በዚሁ መልክ በኮሜርሻላይዜሽን ክላስተር ውስጥ አስራ አምስት ፕሮጀክቶች አሉን። የምንሠራው ይሔንን ሲሆን፤ ከዛ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት ሽግግር (ኢትዮጵያን ፉድ ሲስተም ትራንስፎርሜሽን) ላይም እንሠራለን። እዚህ ላይ በርካታ ሚኒስትሮች የሚገኙበት ሲሆን፤ እርሱንም እናግዛለን።

የዲጂታል ግብርናን እናስተባብራለን። የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ እርሱንም ለማስተግበር፤ እያስተባበርን እና ሁሉንም አካላት እያሳተፍን አዋጅ ደንብ እና መመሪያዎች እንዲወጡ እያደረግን ነው። ስለዚህ በአጠቃላይ ችግር ከመለየት ጀምሮ መፍትሔ እስከ ማመንጨት በማገዝም ሆነ በመምከር እንዲሁም በማስተባበር እንሠራልን። ሥራችን እና ኃላፊነታችን ከግብርና በላይ ሰፊ ነው። ማምረት ብቻ ሳይሆን ገበያንም አካቶ ይይዛል። ኢንዱስትሪ እና መስኖን የሚይዝ ሲሆን፤ እነዚህ በሚኒስትር ደረጃ ከሚታዩት በተጨማሪ፤ ኅብረት ሥራ ላይ፤ ኢንቨስትመንት ላይ እንሠራለን። እነዚህን ሁሉ አንድ ላይ በማቀናጀት ከግብርና ምርት ግብዓት ጀምሮ እስከ ሸማቹ ጠረጴዛ ድረስ እናስተሳስራለን። ለዚህ ደግሞ የተለያዩ መድረኮች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ጥናት እናደርጋለን ብላችኋል። ከግብርና ጋር ተያይዞ በዋናነት ያጠናችኋቸውን ይግለፁልን?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ለማምረት ሁለት ነገሮች ወሳኝ ናቸው። አንደኛው አፈር ሲሆን፤ ሁለተኛው ውሃ ነው። አጠቃላይ የሀገሪቷን የአፈር መዋቅር ለይተናል። አጠቃላይ የአፈርን ለምነት እና አሲዳማነት አውቀናል። የትኛው ቦታ ምን ዓይነት አፈር እና ምን ዓይነት ማዳበሪያ ይፈልጋል የሚለውን በጥናት ለይተን በዛው ልክ ምክረ ሃሳብ አስቀምጠን እና በምርምር ለክተን እየሠራንበት ነው። በውሃ በኩልም ጥናት ላይ ተመሥርተን ሠርተናል።

ከመሬት በላይ የሚታየውን ውሃ ሳይሆን የማይታየውን የከርሰ ምድር ውሃ ላይ ጥናት በማድረግ የት ቦታ ምን ያህል ውሃ አለ? በውሃ አማካኝነት ምን ያህል መሬት ማልማት ይቻላል? የሚለውን ማወቅ ወሳኝ ነው። በተጨማሪ ፖሊሲ ላይ እና ስትራቴጂ ነደፋ ላይ ጥናት እናደርጋለን።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹ከፋይናንስ አቅርቦት ቀጥሎ የግብርናው...

**ከገጽ 7 የዞረ**

የመሥሪያ ቤቶች አቅም ማለትም ግብርና ላይ ለሚሠሩ፣ ኢንቨስትመንት ላይ የሚሠሩ ተቋማትን ምን ይመስላሉ? የት ቦታ ምን ችግር አለባቸው? ክልሎች እና ኅብረት ሥራዎችም አደረጃጀታቸውም ሆነ አተገባበራቸው ላይ ምን ቢደረግ ይሻላል? ብለን እናጠናለን፡፡ የመንግሥት ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ የግል ተቋማትንም እናግዛለን፡፡ የእኛ ፍላጎት ለውጥ ነው፡፡ ሀገሪቷ መድረስ ያለባት ቦታ ላይ እንድትደርስ የግብርናም ሆነ ሌሎች ተቋማት እናጠናለን። ለምሳሌ ዘር ላይ የሚሠራ ተቋም ምን መምሰል አለበት? የፌዴራል እና የክልል እንዲሁም የግል ዘር ላይ የሚሠሩ ሁሉንም ተቋማት እንተነትናለን፡፡ የማንገባበት የለም፡፡ በሁሉም በኩል እናግዛለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ጥናቶች ካጠናችሁ በኋላ ትግበራው እና ምክረ ሃሳብ ተቀብሎ ተግባራዊ በማድረግ ዙሪያ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** እስከ አሁን ካጠናናቸው ጥናቶች እና ካቀረብናቸው የመፍትሔ ሃሳቦች መካከል 65 በመቶ አካባቢ ተግባር ላይ ውሏል፡፡ ጥናቱ ለአንዳንድ ተቋማት አሠራራቸውን እንዲከልሱ አድርጓቸዋል። ተግባራዊ የማያደርጉት ጥቂቶች ናቸው፡፡ የምንነሳው ከተግባራዊ ችግር እና ከእነርሱ ጥያቄ ስለሆነ ወዲያውኑ ጥናቱ ላይ በመመሥረት ወደ ተግባር ይገባል፡፡ አሁን የባሕሪ (ካራክተራይዜሽን) ጥናት እያደረግን ነው። የሶማሌ እና የደቡብ ምዕራብ ክልሎች የግብርናው ዘርፍ ውጤታማ የሚሆንላቸው በምን መልክ ነው? ብለን ጥናት አጥንተናል። ለሲዳማ አሁን እየሠራን ነው። ለብዙዎች ሠርተናል፡፡ በተለይ የቴክኒክ ድጋፍ ለሚፈልጉ ክልሎች እናግዛለን፡፡ የት ቦታ ትኩረት ቢያደርጉ የተሻለ እንደሚሆን እና አሁን በሚሠሩት ሥራ ምን ዓይነት መሰናክል እንደሚያጋጥማቸው እንጠቁማለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በሥራችሁ ሒደት ግብርና ዘርፍ ላይ አለ የምትሉት ትልቅ ችግር ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ ፡-** ትልቁ ለማንኛውም ችግር መፍትሔ ማግኛ ቁልፉ ፋይናንስ ነው፡፡ ፋይናንስ ለእኛ አይደለም። ይህንን ሥራ ለማስኬድ የብድር አቅርቦት ይፈልጋል፡፡ ሁሉም አርሶ አደር አቅም የለውም፤ ወይም አቅም አለው ማለት አይቻልም፡፡ ነገር ግን በግለሰብ ደረጃ አንድ አርሶ አደር ትራክተር ይገዛል ማለት ከባድ ነው። አርሶ አደሮችን አሰባስቦ ትራክተር እንዲገዙ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን ይህንን የመሥሪያ የሕግ ማዕቀፍም ሆነ ምንም ዓይነት መንገድ የለም፡፡ ስለዚህ የብድር አቅርቦት ይፈልጋሉ። እንኳን ትራክተር ዘርም ሆነ ማዳበሪያ ለመግዛት ብድር የሚፈልጉ አርሶ አደሮች አሉ፡፡ ምንም ብድር የማይፈልጉም አሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኛው አርሶ አደር ብድር ይፈልጋል፡፡ ይህ ትልቅ ችግር ነው፡፡

ከፋይናንስ አቅርቦት ቀጥሎ የግብርናው ዘርፍ ትልቅ ችግር የማከማቻ መዋቅር አለመኖር ነው፡፡ ሰው ያመርታል፤ ብዙ ጊዜ እና ጉልበት ፈሶበት የተመረተው ምርት በአንድ ቀን ዝናብ ከጥቅም ውጪ ይሆናል፡፡ ተሰብስቦ ሜዳ ላይ ቢደረግ በአንድ ቀን ሌሊት ብዙ የተለፋበት የሚበላሽበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ በየገጠሩ የማከማቻ መጋዘን ያስፈልጋል። አንዳንዴ መጋዘን ቢኖርም በየቦታው ባሉ መጋዘኖች ለማስቀመጥ ዋስትና የለም፡፡ አላየሁም ቢባል ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡ አብዛኛው ሰው በሃይማኖት ውስጥ በመታሠሩ እና እምነት ስለሚዘው እንጂ ወንጀል የሚሠራበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ መፍትሔው ሰዎች በከተማ ቡና እና ሻይ ቤቶች ወይም ሆቴሎች ለመሥራት ከመረባረብ ይልቅ፤ ገጠር መጋዘን ቢሠሩ ለዛም ሥርዓት ቢበጅ በአገሪቱ ትልቅ ለውጥ ማምጣት ይቻላል፡፡

ምርት ሲበላሽ የሚጎዳው አንድ አርሶ አደር ብቻ አይደለም፡፡ ምርቱ በመበላሸቱ አቅርቦት ያንሳል፤ በዚህ ጊዜ ሸማቹም ላይ የሚሸምተው ምርት ዋጋ የተጋነነ ይሆንበታል። ስለዚህ ትርጉሙ ትልቅ ነው፡፡ ይህንን ችግር መቅረፍ እንዲቻል ገጠር ውስጥ እንደዛ አይነት መጋዘኖች ቢሠሩ መልካም ነው። አነስተኛ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያዎችም ቢሠሩ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ግን የብድር አቅርቦት ወሳኝ ነው። ትልቅ የእህል ማከማቻ መጋዘን ለመሥራት አቅም ላይኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ብድር ቢኖር ተበድሮ በየወሩ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ ብድሩ ሊመለስ ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ባንኮች ሲታዩ በአጠቃላይ ስሪታቸው ከተማ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ለገጠር እና ለረዥም ጊዜ የሚሆን ገንዘብ አያበድሩም፡፡ ዋስትና ይፈልጋሉ፡፡ በሬ ተቆጥሮ ዋስ አይሆን፤ ያለው ቤት ብቻ ነው፡፡ ቤቱም ቢሆን የሣር ይሆናል፡፡ ዋጋ ላያወጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ አርሶ አደሩ ለብድር የተለየ መንገድ ይፈልጋል፡፡ እነዚህ ሁለት ችግሮች ከተቀረፉ ትራክተሩ ይመጣል፤ እሴት የሚጨምር አግሮ ኢንዱስትሪው ይመጣል፡፡ በዓለም አቀፍ ገበያ ውስጥም ጥሩ ተወዳዳሪ እንሆናለን፡፡



**አዲስ ዘመን፡- ግብርናውን እያስተጓጎሉ ካሉ የተለያዩ ምክንያቶች መካከል አንዱ የግብዓት አቅርቦት ነው፡፡ ስግብዓት አቅርቦት 325 ሱቆች እንዳሉ ተናግረዋል፡፡ ሱቆቹ ራሳቸው በእርግጥ ለአርሶ አደሩ በቂ ግብዓት ማቅረብ ይችላሉ?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** በእርግጥ አቅርቦቱ ከአንድ ቋት ነው። የሚከፋፈል እንጂ ራሳቸው የሚያመጡት አይደለም፡፡ አሁን ከተመሳሳይ ቦታ እየመጣ ነው፡፡ እኛ ግን የምንፈልገው ራሳቸው አስመጥተው እንዲያከፋፍሉ ነው፡፡ ነገር ግን ያንን ለመሥራት አቅም የላቸውም። እነዚህ ሱቆች ለየብቻ ሳይሆን ማኅበር ፈጥረው ተደራጅተው አስመጥተው እንዲያከፋፍሉ እንፈልጋለን፡፡ በጋራ ሲሠሩ የራሳቸው መገናኛ መሥመር ይኖራቸዋል፤ ማለት ነው፡፡ ከመንግሥት ብቻ አይጠብቁም። የግል ዘርፉ መጠናከር ይፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በመካናይዜሽን እርሻን ማከናወን ላይ እያጋጠመ ያለው ችግር ምንድን ነው ?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ዋናው የኦፕሬተር ችግር ነው፡፡ አርሶ አደር ወይም የአርሶ አደር ልጆች በዛ ላይ ዕውቀቱም ክህሎቱም የላቸውም፡፡ ይህ ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ ነገር ግን ለእዚህ ችግር መፍትሔው ማሠልጠኛ ማዕከላትን አቋቁመናል፡፡ ስለዚህ በአጭር ጊዜ ብዙ ሠልጣኝ በማፍራት ኦፕሬተሮች እና ቴክኒሻኖች እንዲኖሩ እየሠራን ነው፡፡ በዛ አካባቢ የእውቀት ችግር መኖሩ የሚካድ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የእናንተን ሥራ የሚያከናውኑ ብዙ ተቋማት አሉ፡፡ ደጋፊው ማን ነው?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** እምንደግፈው እኛ ነን። መሠረት እንጥል እና በዛ መሠረት ላይ እንዲሠሩ እናደርጋለን። ለምሳሌ የአፈር ምርመራ እናካሂዳለን፡፡ ከዛ ለአፈር ምርምር ተቋም የተመረመረውን ለኩ እንላለን ከዛ ምርምሩ ልክ ነው ወይ? በዝቷል ወይስ አንሷል? የሚለውን ይለካሉ፡፡ በዚህ መልክ ወደ 500 አካባቢዎች ሠርተዋል፡፡ ሌሎችም ተቋማት መሠረት ስንጥልላቸው ማረጋገጡን ደግሞ እነርሱ እየሠሩ ይሔዳሉ፡፡ ስለዚህ ሥራችን ተቋማትን ማብቃት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሰሞኑን የዋጋ መረጃ ማሳወቅ የሚያስችል ቴክኖሎጂ አርብቶ አደሩ በስልኩ የሚያገኝበት ሁኔታ ላይ ስመሥራት ስምምነት ፈርማችኋል፡፡ እስኪ ስለዚህኛው ጉዳይ በደንብ ያብራሩልን?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ሥራችን እስከ ግብይት ድረስ የዘለቀ ሲሆን፤ መረጃው ግብይትን የተመለከተ ብቻ ሳይሆን ከእንስሳት ጋር ተያይዞ ብዙ መረጃዎችን የሚሠጥ ነው። ገበያዎች ባሉበት ቦታ ላይ በየወረዳው የእኛ ባለሙያዎች በመኖራቸው የገበያ ጥናት ያካሒዳሉ፡፡ ያንን ካካሄዱ በኋላ መረጃ ሲያቀብሉ በዋናው የመረጃ ማዕከላችን ይታያል። ማንኛውም ሰው በ‹‹6077›› ደውሎ እነዚህን መረጃዎች ያገኛል፡፡ በእኛ በ157 ወረዳዎች ውስጥ በየገበያ ማዕከላት መረጃ ይሰበሰባል፡፡ ይኸው መረጃ ተመልሶ ይሠራጫል፡፡ የሚሰራጨው ለአርብቶ አደር ለከፊል አርብቶ አደር ወይም ለአርሶ አደር ብቻ ሳይሆን ለሚገዛ ሸማችም ጭምር ነው። የቄራ አገልግሎት ለሚሰጡ ሁሉ ነው፡፡ የት ቦታ በምን ዓይነት ዋጋ እንደሚሸጥ ያንን ያሳያል፡፡

ሰብል የሚመረትባቸው ቦታዎች ላይ የሰብሎቹን ዓይነት ጥራት እና ዋጋቸውን እንሠበስባለን፤ ይህንኑ መረጃ እናሰራጫለን ማለት ነው፡፡ ይሄ አርሶ አደሮች ያለአግባብ ምርታቸውን እንዳይሸጡ፤ ሸማቾችም ምርቶችን ያለአግባብ ዋጋ እንዳይከፍሉ ያደርጋል፡፡ ይሔ ለአምራቹም ለሸማቹም የመረጃ ሥርዓት የመገንባት እና አገልግሎት የመስጠት ሒደት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ሥራ እስከ አሁን ነበረ፤ ወይስ አሁን ገና አዲስ ነው?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** አይ የአሁኑ ስምምነት ሥራውን ለማስፋት ነው እንጂ፤ እስከ አሁንም እየሠራን ነበር። ለረዥም ጊዜ ተሠርቶባቸዋል፡፡ ‹‹8028›› ላይም አርሶ አደሮች እንዲያመርቱ እንስሳትን እንዴት እንደሚያደልቡ፤ ጤናቸውን እንዴት እንደሚጠብቁ አገልግሎት ይሠጣል። በቀጣይ ደግሞ ተጨማሪ ቦታዎችን እንድንሸፍን ስምምነት ላይ ደርሰናል። አዲሱ ስምምነት የአፋርን ክልል የሚጨምር ነው። ይህ ከቋንቋ ጋር ይገናኛል፡፤ ለምሳሌ ደጋ ላይ ላሞች በጎች ፍየሎች ሲሆን፤ ቆላ ሲኬድ ደግሞ ግመል እና ሌሎችም የጋማ ከብቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ አካባቢ ሲቀየር ቋንቋ ብቻ ሳይሆን የእንስሳ አይነቶቹ፤ የባለሙያ አይነቶ፣ ምክሩም ይቀየራል። መጀመሪያ ሲደወል ቋንቋ ይመረጣል፤ ከዛ እንስሳም ሆነ ሰብል ምን ዓይነት እንደሆነ እና በየት አካባቢ እንዳሉ ሲገልፁ ማማከሩ ይቀጥላል፡፡

ይህንን በጋራ ከሌሎች ጋር የምንሠራው ሲሆን፤ ቀደም ሲል ከሜሪሲ ጋር በጋራ ሶማሌን አካተናል፡፡ ይህ ከአርብቶ አደሮች ጋር በጋራ እንድንሠራ የሚያደርገን ሲሆን፤ ፊድ ዘፊውቸር ከተሰኘ ድርጅት ጋር ያደረግነው ስምምነት ደግሞ ገበያን በተመለከተ በጋራ ለመሥራት ነው፡፡ ከእነርሱ ጋር አሁን ያሉንን 157 ወረዳዎች ወደ 250 ወረዳዎች ከፍ ማድረግ የሚስችለን ነው፡፡ ይህ ተደራሽታችንን እያሰፋን እንድንሔድ የሚያስችል ስምምነት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አርብቶ አደሩ አካባቢ በእርግጥ ምን ያህል በስልክ ጥሪ ወይም በዲጂታል መንገድ ተደራሽ መሆን ይቻላል?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ደጋ ላይ ከምናገኛቸው አርሶ አደሮች የበለጠ ለመረጃ ቅርብ የሚሆኑት አርብቶ አደሮች ናቸው። ዲጂታል መድረክ ስንከፍት ፈጥነው የማግኘት እና የመጠቀም ሁኔታቸው በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ አርሶ አደሮች በተለያየ መንገድ በማኅበራዊ ግንኙነታቸው በቤተክርስቲያን፣ በመስኪድ እና በዕድር በመሳሰሉት በተለያዩ የመገናኛ አጋጣሚዎች መረጃ ይለዋወጣሉ። አርብቶ አደሮች ግን ተራርቀው ስለሚኖሩ የሚገናኙት በዲጂታል መንገድ ነው። ለመረጃ በጣም ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጡ ሲሆን፤ በሁለት ዓመት ውስጥ 350 ሺህ አካባቢ ደርሰዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡-በዲጂታል ወይም በሞባይል አገልግሎት የምትሰጡባቸው ክልሎች ስንት ነበሩ?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** አራቱ ዋና ዋና የተሰኙት ክልሎች ላይ ብቻ ነበር፡፡ አሁን ሰባት ደርሰዋል፡፡ አሁንም በዚያ አይገደብም፡፡ የትም ቦታ ሆኖ ኔትወርክ ባለበት ‹‹8028›› ላይ ቢደወል መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡ ነገር ግን አሁን መረጃ የምንሰበስበው ከሰባቱ ክልሎች ነው፡፡ አሁን ግን ከእዛ ወጥተን ወደ አርብቶ አደሩም እየገባን ነው፡፡

የኢንስቲትዩቱ የመጨረሻ ግቡ ምርታማነትን ማሳደግ ነው፡፡ ምርት የሚቀንሰው በተባይ ወይም በበሽታ ከሆነ ምርቱ ሳይበላሽ ወይም ሳይቀንስ አስቀድሞ የሚከላከልበት ምክረ ሃሳብ ይሰጣል፡፡ ሥራው ምርት ከፍተኛ እንዲሆን ማድረጊያ እና ገቢ ማሳደጊያ ነው፡፡ ስለዚህ የመጨረሻ ግቡ የአርሶ አደሩን ምርታማነት እና ገቢ መጨመር ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ ሲጨምሩ የአርሶ አደሩ ሕይወት የተሻለ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የገጠሩን ማኅበረሰብ ኑሮ ማሻሻል ላይ እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እስከ አሁን አገልግሎት እያገኙ ያሉ ምን ያህል አርሶ አደሮች አሉ?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** እስከ አሁን ‹‹ 8028 ›› ላይ በመደወል ብዛት ላለፉት ሦስት ዓመታት ወደ 50 ሚሊዮን አካባቢ የስልክ ጥሪዎች የተስተናገዱ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል በተደጋጋሚ የሚደውሉ እና መረጃ እያገኙ ሥራቸውን የሚያሻሽሉ ወደ ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቋሚ ደዋይ አርሶ አደሮች አሉ። ከንግድ ጋር በተያያዘ ‹‹6077›› ላይም አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን አካባቢ ደዋይ አለ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ክፍያ ከተሰኘ ተቋም ጋርም ስምምነት አድርጋችኋል፡፡ ስምምነቱ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** ስምምነቱ የገቢ ደረሰኝ ሥርዓት (ኢንፑት ቮቸር ሲስተም) ላይ ያተኮረ ነው፡፡ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ ሲገዙ በብሔራዊ ደረጃ ግብርና ሚኒስቴር ማዳበሪያ ይገዛል፡፡ የገዛውን ማዳበሪያ ለዩኒየን ወይም ለኢትዮጵያ ኅብረት ሥራዎች ኮርፖሬሽን ያደርሳል፡፡ አርሶ አደሩ ጋር እስከሚደርስ ድረስ የሚሔደው በዱቤ ነው። ዩኒየኖቹ ገንዘቡን ሲሰበስቡ አንዳንዴ ቶሎ ይገባል። አንዳንዴ ሌላ ነገር ይሠሩበታል፡፡ የገንዘብ ብክነት እና መዘግየት ነበር፡፡ ስለዚህ አሁን ክፍያ የሚደረገው ለፋይናንስ ድርጅቶች ለባንክ ወይም ለቁጠባ ድርጅት እንዲሆን እየተስማማን ነው፡፡ ይሔ ሲደረግ ክፍያው መፈፀሙን በራሪ ደረሰኝ ይሰጣቸዋል፡፡

አርሶ አደሮች ደረሰኙን ይዘው ወደ ዩኒየን ይሔዳሉ። ዩኒየኑ ደረሰኙን አይቶ ማዳበሪያ ይሠጣቸዋል፡፡ ስለዚህ ዩኒየኑ በማዳበሪያ ዙሪያ ከገንዘብ ንክኪ ነፃ ይሆናል። ይህንን በቅድሚያ በወረቀት ሠርተን ጨረስን፤ ወደ ሰባት ሚሊዮን አርሶ አደሮች ይጠቀሙበታል፡፡ የገንዘብ እንቅስቃሴው ወደ 32 ቢሊዮን ብር የሚደርስ ሲሆን፤ ይህንን ዲጂታል ለማድረግ አቅደን ሠርተናል፡፡

ከዚህ በኋላ አርሶ አደሩ በቅርብ ርቀት ባለ የገንዘብ ተቋም በባንክ ወይም በአንድ ሌላ የገንዘብ ድርጅት ይከፍላል፤ ደረሰኙን ሲይዝ በዲጂታል መንገድ ዩኒየኑ መከፈሉን ያረጋግጣል፡፡ አርሶ አደሩ ዩኒየኑ ቅርብ ከሆነ ሄዶ ይወስዳል፡፡ ቅርብ ካልሆነ ቤቱ ድረስ ይመጣለታል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ?**

**ዶ/ር ማንደፍሮ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## በሽርክና አቅምን በማጎልበት አምራችነትን የማሳደግ ጥረት

አንተነህ ቸሬ

መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል ተብሎ ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት አንዱ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሦስት ዋና ዋና መሰረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። እነዚህ ተልዕኮዎቻቸውም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን ማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማከናወን ናቸው።

ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው ኅብረተሰብ ስራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሰረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ፡፡

ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም ርካሽ የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና  የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ  ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በመላ ሀገሪቱ በመንግስት ብቻ የተገነቡ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን፣ በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ። ፓርኮቹ የተሻለ የመሰረተ ልማት አቅርቦትና የአገልግሎት አሰጣጥ ያላቸው ስለሆኑ፣ ሀብቶቻቸውን በማቀናጀት በሽርክና (Joint-Venture) ተጣምረው በእነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰማሩ ኩባንያዎች ቁጥራቸው እያደገ ነው፡፡

‹‹ኢዜድኤም›› ንግድና ኢንቨስትመንት (EZM Trade and Investment) ሀገር በቀል የተባለ ድርጅት፣ የፕላስቲክ ቱቦዎችን በማምረት የ27 ዓመታት ልምድ ካለው የቻይናው ‹‹ሪፎ›› (RIFENG Enterprise - FOSHAN) ኩባንያ ጋር በሽርክና (Joint-Venture) በመተባበር ከቻይና የሚገቡ የፕላስቲክ ቱቦዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችለውን ፋብሪካ ሰሞኑን በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ስራ አስጀምሯል፡፡ የ‹‹ኢዜድኤም›› እና ‹‹ሪፎ›› ሽርክና ሁለቱ ኩባንያዎች የ‹‹ሪፎ››ን ምርቶች በሀገር ውስጥ በማምረት ለኢትዮጵያና ለዓለም አቀፍ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ በሦስት ሺ ካሬ ሜትር መሬት ላይ ተገንብቶ ስራ የጀመረው ፋብሪካ፣ በ14 ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር የተገነባ ነው፤ ፋብሪካው ከውጭ የሚገባውን የፕላስቲክ ቱቦ ምርት በሀገር ውስጥ ለመተካትና ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ ይዞ እንደሚሰራም ተነግሯል፡፡ የኩባንያዎቹ ሽርክና በዘመናዊ መልኩ የተነደፉ፣ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውና ለአካባቢ ሥነ-ምኅዳር ተስማሚ የሆኑ የመጠጥ ውሃና እና የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎችን ለማምረት ያስችላል፡፡

ፋብሪካው በዓመት እስከ ሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ፒፒአር (PPR) ቱቦዎችን፣ አንድ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ የፒፒአር (PPR) መገጣጠሚያዎችን፣ አንድ ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የፒቪሲ (PVC) የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎችን፣ ዘጠኝ መቶ ሺ የፒቪሲ (PVC) መገጣጠሚያዎችን እንዲሁም ከሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሜትር በላይ የፒቪሲ (PVC) ኮንዱዩት ማስተላለፊያ ቱቦዎችን የማምረት አቅም አለው፡፡

የ‹‹ኢዜድኤም›› (EZM) ንግድና ኢንቨስትመንት ኩባንያ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ እስመለዓለም ዘውዴ፣ ኩባንያው በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ስራ መግባቱን ጠቁመው፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኩ ሼድ በተከራየ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ሰራተኞችን አሰልጥኖና ማሽኖችን ተክሎ የምርት ስራ መጀመሩን ይናገራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፣ የፋብሪካው ምርቶች ለኮንስትራክሽን ስራ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ቱቦዎች ሲሆኑ፣ ከውጭ የሚገባውን የፕላስቲክ ቱቦ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚደረገውን ጥረት ከግብ ለማድረስ ያስችላሉ፡፡ ፋብሪካው አሁን ባለው አቅም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን የፕላስቲክ ቱቦ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ይችላል። ፋብሪካው በዓመት 17 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን የሚያመርት ሲሆን፣ ከምርቱ 50 በመቶውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብም አቅዷል፡፡

ፋብሪካው ዓለም አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟሉ የፕላስቲክ ቱቦዎችን እንደሚያመርት የሚናገሩት ዋና ስራ አስፈፃሚው፣ በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ምርቶች ቻይና ውስጥ ከሚመረቱትና ለውጭ ገበያ ከሚቀርቡት ምርቶች ጋር አንድ ዓይነት እንደሆኑና ተመሳሳይ የጥራት ማረጋገጫ እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡ ኩባንያው ወደ አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብቶ መስራቱ ብዙ ጥቅሞችን እንዳስገኘለትም አቶ እስመለዓለም ያስረዳሉ፡፡

‹‹ፋብሪካው በሦስት ፈረቃዎች ለ24 ሰዓታት የሚሰራ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለ200 ሰዎች ቋሚ የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ በንግድ ትስስርና በሌሎች አማራጮች ለ400 ዜጎች ተጨማሪ የሥራ ዕድሎችን አቅርቧል። ፋብሪካው የምርት አቅሙ ሲጨምር ተጨማሪ የሥራ እድሎችን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ድርጅቱ በአፍሪካ ውስጥ አስተማማኝና ቀዳሚ ተመራጭነት ያለው የፕላስቲክ ቱቦዎችና መገጣጠሚያዎች ማምረቻ ኩባንያ ለመሆን በሚያስችለው አቅም ላይ ይገኛል›› ይላሉ፡፡

የ‹‹ሪፎ›› ኢንተርናሽናል ስራ አስኪያጅ ጄሰን ቻን በበኩላቸው፣ ኩባንያው የፕላስቲክ ቱቦዎችን በማምረት የብዙ ዓመታት ልምድ እንዳለውና ስራውንም በበርካታ የዓለም አገራት እያስፋፋ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ከደቡብ አፍሪካ በመቀጠል በአፍሪካ ሁለተኛዋ የኩባንያው መዳረሻ እንደሆነች ተናግረዋል። አገሪቱ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ ከሆኑ አገራት መካከል አንዷ በመሆኗ የኩባንያው ምርጫ መሆኗንም ጠቁመዋል፡፡ ኩባንያው ከ‹‹ኢዜድኤም›› ጋር በጀመረው ሽርክና ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ምርቶች ተመርተው ለገበያ እንደሚቀርቡ ይገልፃሉ፡፡

ፋብሪካው በአጭር ጊዜ ማሽኖችን ተክሎና ሰራተኞችን አሰልጥኖ ወደ ስራ የገባ ድርጅት እንደሆነ የሚናገሩት የአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ስራ አስኪያጅ አቶ ጉልላት አበበ፣ የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ዘርፍ በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመሆኑ የፋብሪካው ምርቶች ለዘርፉ እጅግ አስፈላጊ ግብዓቶች ናቸው ብለዋል፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት በፓርኩ ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች ከ50 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንደተገኘም አቶ ጉልላት ይናገራሉ። ‹‹ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች የተገኘው ገቢ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ማዳን ከተቻለው እና ለሀገር ውስጥ ገበያ ከቀረበው ምርት ከተገኘው ገቢ ጋር ሲደመር ኢንዱስትሪ ፓርኩ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እያስገኘ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡›› ያሉት ስራ አስኪያጁ፣ የ50 ሚሊዮን ዶላሩን ገቢ ማሳካት የተቻለው በአምስት አምራቾች ብቻ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ፓርኩ ከስምንት ሺ በላይ ለሆኑ ዜጎች የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ አሁን በፓርኩ ውስጥ 13 አምራቾች አሉ፤ እነዚህ ሁሉ ማምረት ሲጀምሩ ከውጭ ምንዛሬና  ከሀገር ውስጥ ግብይት የሚገኘው ገቢም ሆነ የሚፈጠረው ስራ እድል ይጨምራል፡፡

በፓርኩ ውስጥ የሚገኙ አምራች ኩባንያዎች በመደበኛነት ከሚያከናውኗቸው የምርት፣ የስራ እድል ፈጠራና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት ባሻገር፣ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት ረገድም የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ እንደሚገኙ ዋና ስራ አስኪያጁ ይናገራሉ፡፡ ‹‹ኩባንያዎቹ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ትኩረት መስጠት የሚገባቸው በመሆኑ ላይ አስፈላጊው ግንዛቤ አላቸው›› የሚሉት አቶ ጉልላት፣ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ ባለሃብቶቹ ትምህርት ቤቶችን ማደሳቸውንና ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረጋቸውን ይገልፃሉ፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ‹‹የ‹ኢዜድኤም› እና ‹ሪፎ› የጋራ ትብብር የውጭና የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች በሽርክና (Joint-Venture) የሚሰሩበት የቢዝነስ ሞዴል እድገት እያሳየ እንደሆነ ጠቋሚ ነው›› ይላሉ። ሀገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅም አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸው ውጤት እያስመዘገበ ስለመሆኑ እንደሚያመላክትም ይገልፃሉ፡፡

ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው የሚያመርቱ ኩባንያዎች ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ከሚያበረክቱት አስተዋፅዖ በተጨማሪ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግርን እውን በማድረግ የሚኖራቸው ሚናም የላቀ እንደሚሆን ይናገራሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው የሚያለሙ ኩባንያዎች ለዜጎች የስራ እድል የመፍጠር ፋይዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖርና የምርት ተግባራት በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም የምርት ስራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛሉ፡፡

እንደ ዋና ስራ አስፈፃሚው ገለፃ፣ ባለፉት አራት ዓመታት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ተመርተው ወደ ውጪ አገራት ከተላኩ ምርቶች ከአንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ተገኝቷል። በተኪ ምርቶች አማካኝነት ደግሞ 550 ሚሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማዳን ተችሏል። በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች ከተገነቡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የጨርቃ ጨርቅ፣ የግብርና፣ የፕላስቲክና ሌሎች  ምርቶች ለውጭ ገበያ እየቀረቡ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ‹‹የኢንቨስትመንት ዘርፍን ለማሳደግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ጥራቱን የጠበቀና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው አገልግሎት እየተሰጠ ነው›› የሚሉት ዋና ስራ አስፈፃሚው፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያመርቱ ኮርፖሬሽኑ በትኩረት ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ ይናገራሉ፡፡ ባለሀብቶች በርካታ ጥቅሞችንና እድሎችን ወደያዙት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲሰማሩም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል። የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች በመፍታትና አፈፃፀማቸውን በማሻሻል መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ማሳካት ይገባል።

በጦርነት ቀጣና ውስጥ የነበሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች በሙሉ አቅማቸው ወደ ምርት ስራቸው እንዲመለሱ ለኢንቨስትመንት ዘርፉ መነቃቃትና ማንሰራራት ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የድህረ ጦርነት የኢንቨስትመንት ማነቃቂያ ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀትና በብቃት መተግበር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ጥረት ውስጥ ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶችና ከውጭ ኩባንያዎች ጋር በሽርክና ለሚሰሩ ሀገር በቀል ድርጅቶች ልዩ ድጋፍ ማድረግም ሊዘነጋ አይገባም፡፡

**የፋብሪካው ምርቶች ለኮንስትራክሽን ስራ በግብዓትነት የሚያገለግሉ ቱቦዎች ሲሆኑ፣ ከውጭ የሚገባውን የፕላስቲክ ቱቦ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚደረገውን ጥረት ከግብ ለማድረስ ያስችላል፡፡ ፋብሪካው አሁን ባለው አቅም ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን የፕላስቲክ ቱቦ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት ይችላል፡፡ ፋብሪካው በዓመት 17 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጡ ምርቶችን የሚያመርት ሲሆን፣ ከምርቱ 50 በመቶውን ለውጭ ገበያ ለማቅረብም አቅዷል**

# ጎሜ

# በሕዝብ ስም የማለ ሁሉ የሕዝብ ወዳጅ አይደለም

**አሲ ሴሮ**

አብዛኞቹ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ‹‹ሀሁ››ን የሚጀምሩት በሕዝብ ስም በመማል ነው። መነሻም ሆነ መድረሻቸው ሕዝብ እንደሆነና ለሕዝብ ጥቅም ሲሉም ሕይወታቸውን አሳልፈው እንደሚሰጡ ሲምሉና ሲገዘቱ መስማት አዲስ አይደለም፡፡ እንደውም የጀማሪ ፖለቲከኛ መለያ እስከመሆን ደርሷል፡፡

ከየትኛውም ፖለቲከኛ አንደበት ከማይጠፉ ቃላት ውስጥ ሕዝብ የሚለው ተጠቃሽ ነው፡፡ ሕዝቡ ከእነዚህ ፖለቲከኞች የተጠቀመው ነገር ባይኖርም ፖለቲከኞቹ ግን በሕዝብ ስም ብዙ ተጠቅመዋል። አንዳንዶቹ የኑሮ መሰረታቸው አድርገው ስለሚወስዱትም የዕለት ኑሯቸውን ከመምራት አንስቶ ሕይወታቸውን እስከመለወጥ ያስቻለ ሃብት ለማፍራት በቅተዋል፡፡

ትላንት በባዶ እግሩ ሲኳትን የምናውቀው ፖለቲከኛ የሕዝብን ስም ጠርቶ ዘመኑ ባመጣው አውቶሞቢል ሲንፈላሰስ በአይናችን በብረቱ ተመልክተናል፡፡ በተለይም የአሁን ዘመኖቹ ፖለቲከኞች ሕዝብ የሚለው ጥቅል መጠርያ አንሶባቸው ብሔርን እና ኃይማኖትን ጭምር ደርበው የበለጠ ሕዝባዊነታቸውን ሲያፋፍሙ እየተመለከትናቸው አንዳንዴም እየታዘብናቸው ነው።

ሆኖም እነዚህ ሕዝበኞች ያሰቡትን እስኪያሳኩ እና የማይጠረቃ ፍላጎታቸውን እስኪሞሉ ድረስ ትዝብትም፤ ወቀሳም የሚበግራቸው አይደሉም። ጭራሽ እራሳቸውን የሰቀሉበት ማማ የትየለሌ ስለሆነ እነሱ ተነኩ ማለት ሕዝብ ተነካ ማለት ነው። ማንን ሳይሾማቸውና ሳይቀባቸው የሕዝብ መሪ፤ ጠበቃና ተሟጋች አድርገው እራሳቸውን ስለፈረጁ እነሱን መንካት ማለት ምልዓተ ሕዝቡን እንደመንካት ይቆጥሩታል፤ ወይንም እንዲቆጠር ይፈልጋሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ከሚታወቅባቸው አኩሪ ባሕሪያቶቹ መካከል የሚጠቀሱት፣ ሕግ አክባሪነቱና ሰላም ወዳድነቱ ናቸው፡፡ ከሕግ አክባሪነቱና ከሰላም ወዳድነቱ ጋር ደግሞ ለዘመናት በጋራ የገነባቸው ትውልድ ተሻጋሪ ማኅበራዊ እሴቶቹ ትልቅ ሥፍራ የሚሰጣቸው ናቸው፡፡ እርስ በዕርስ በሚያደርጋቸው የዕለት ተዕለት መስተጋብሮቹ ተዋዶና ተከባብሮ መኖር ብቻ ሳይሆን፣ የብሔርና የሃይማኖት ልዩነቶች ሳይገድቡት በጋብቻ ጭምር የተሳሰረ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ሕዝበኞች ዛሬ ተነስተው ሕዝቡን ስለበዳይና ተበዳይ በትርክት፤ ስለልዩነት፤ ስለመጠፋፋትና መለያየት ሊመክሩት ሲሞክሩ ይደመጣል፡፡

እነሱ የሚያውቁትና የሚያዋጣቸውም ክፉ ምክርና ሃሳብ ስለሆነ በጠበበ ጭንቅላታቸው ጠባብ ሃሳብ ቀን ከሌት ሲተፉ ይደመጣሉ፡፡ አንደበታቸው ላይ የተገጠመው ክፉ ጋኔል ስለሆነ ቆሌያቸው የሚፈልገው ሞት፤ ዕልቅት፤ መፈናቀል እና ስደት የመሳሰሉትን ነው፡፡ ለሺ ዘመናት አብሮ ኖረውን ሕዝብ እርስ በእራሱ እንዲራጠር፤ እንዲገፋፋና ብሎም እንዲገዳዳል በሕዝብ ስም እየማሉ ሴራ ይሸርባሉ፡፡

ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባሕልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው፡፡ የዘመኑ ፖለቲከኞችና አጋፋሪዎቻቸው ግን ለዘመናት የተገነባውን የአብሮነት እሴት በመናድ፣ አንዱ በሌላው ወገኑ ላይ ጭካኔ የተሞላበት ወንጀል እንዲፈጽም መገፋፋት ትልቁ ተግባራቸው ሆኗል፡፡ ልዩነቶችን ጌጦቹ አድርጎ ሳያፍር ለዘመናት አብሮ የኖረ ሕዝብ ውስጥ ጥላቻ በመዝራት ቅራኔ መፍጠር፣ የዘመኑ ትውልድ ባልኖረበት ዘመን ትርክት መወንጀል፣ የገዛ ወገንን መጤና ባለቤት በማለት መከፋፈል፣ ተፈጥሯል ለተባለ ክስተት ዕዳ መክፈያ ይመስል በጭካኔ መጨፍጨፍና ለማመን የሚከብዱ የሰብዓዊ ሙብት ጥሰቶችን መፈጸም ተለምዷል፡፡

> **የብዙዎችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች አመሰራረት ስንመለከተው ከተጠና አመላከት ይልቅ በስሜት ወይም በግብታዊነት የተመሰረቱ ናቸው። የግል ጥቅማቸው አልከበር ሲላቸው፤ ከወቅቱ የፖለቲካ አካሄድ ጋር ሲኳረፉ፤ ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ በአቋራጭ መበልፀግ ሲከጅሉና አንዳንድ ጊዜም እጅ ሲያጥራቸው በድንገት ተነስተው የፖለቲካ ፓርቲ የመሰረቱ ሰዎችን ወይም ቡድኖችን እናውቃለን**

አሁን አሁን ልብ ብሎ ለተመለከተው ለሞት፤ ለአካል መጉደል፤ ለስደትና ለመፈናቀል መንስኤ እየሆኑ ያሉት በሕዝብ ስም በሚምሉ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች አማካኝነት ነው፡፡ እገሌ ብሔር እገሌን በደለ፤ የእገሌ ብሔር የእገሌን ይዞታ ወሰደ፤ የእገሌ ብሔር እገሌን ጨፈጨፈና መሰል የእልቂት እወጃዎች በየቀኑ ሲነዙ ቢውሉም የተባሉት ግፍና ሰቆቃዎች ግን በገሃዱ ዓለም የሉም፡፡

ከራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት ውጪ የሕዝብ ጉዳይ ዴንታም የማይሰጣቸው እነዚህ በሕዝብ ስም የሚምሉና የሚገዘቱ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች ከአጃቢዎቻቸው ውጪ ማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታወቅ ጠብም ሆነ ጥላቻ ባይኖርም የኑሮ መሰረታቸው ነውና እንደዕድር በጡሩንባ ነፊ ሌሊት ተነስተው መርዶ መንገር እንጀራቸው ነው፡፡ የነሱ ኪስ የሚደልበው፤ የኑሮ መሰረታቸው የሚደላደለውና ሕልውናቸው የሚረጋገጠው በሚለፍፉት የመርዶ መጠን ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ ከራሳቸው በፊት ለአገርም ሆነ ለሕዝብ ምንም ደንታ የሌላቸው ስለሆኑ፣ የእነሱ ፍላጎት እስካልተሳካ ድረስ ሚሊዮኖች ቢያልቁ ደንታቸው አይደለም፡፡ እንኳንስ ለወጣቱ መማርና መለወጥ፣ ለአጠቃላይ ሕዝቡ የኑሮ ዕድገት ቀርቶ ለአገር ሕልውናም ደንታ የላቸውም። እነሱ ቀንና ሌሊት የሚማስኑት ለሥልጣንና ይዞት ለሚመጣው ጥቅም ብቻ ስለሆነ፣ የእነሱን ፍላጎት እስካረካ ድረስ ሕዝብና ሀገር ላይ ስለሚመጣው ጉዳት ለአፍታም አይጨነቁም፡፡ አዋጭ ሆኖ ካገኙትም የሸንሸናው ዋና መሐንዲስ ከመሆን አይመለሱም፡፡ በዚህም ምክንያት በሕዝብ ስም እየነገዱ ፍላጎታቸውን ለማርካት ማንኛውንም ወንጀል ይፈጽማሉ፡፡

የብዙዎችን የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች አመሰራረት ስንመለከተው ከተጠና አመላከት ይልቅ በስሜት ወይም በግብታዊነት የተመሰረቱ ናቸው። የግል ጥቅማቸው አልከበር ሲላቸው፤ ከወቅቱ የፖለቲካ አካሄድ ጋር ሲኳረፉ፤ ሰርቶ ከመለወጥ ይልቅ በአቋራጭ መበልፀግ ሲከጅሉና አንዳንድ ጊዜም እጅ ሲያጥራቸው በድንገት ተነስተው የፖለቲካ ፓርቲ የመሰረቱ ሰዎችን ወይም ቡድኖችን እናውቃለን፡፡

አንዳንዶቹም የቤተሰብ አባሎቻቸውን አስተባብረውና ወደ ምር ቦርድ አቅንተው የፖለቲካ ፓርቲ የመሰረቱና ኑሯቸውን ለመደጎም የተጠቀሙበት ግለሰቦች መኖራቸው ጭምርም በየሚዲያው ሲገለጽ የኖረ ነው፡፡ አንዳንዶቹ አሁን የት እንዳሉ ባይታወቅም ከቀድሞው መንግስት እህል እየተሰፈረላቸው ፖለቲካ ማድመቂያ ሆነው መኖራቸው ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም፡፡

እነዚህና መሰል የተበላሸ የፖለቲካ መስመር የሚከተሉ ሰዎችና ቡድኖች በሕዝብ ላይ ኑሯቸውን ለመመስረት አስበው የተነሱ ቢሆንም ከአፋቸው ግን ለሕዝብ ሲሉ እንደተቋቋሙ ከመናገር ቦዝነው አያውቁም፡፡ በንግግሮቻቸው መሀል ያለመታከት ለሕዝብ ያላቸውን ተቆርቋሪነት በመግለጽ አቻ የላቸውም፡፡ ሆኖም ለሕዝብ አንድ ጠብ ያለ ነገር ሲሰሩ አይታዩም፡፡ ሁልጊዜ መውቀስ፤ መተቸት፤ ማብጠልጠል እና ማጠልሸት መለያቸው ነው። ሲያጠለሹና ሲያብጠለጥሉም በበቂ መረጃ ላይ ተመስርተው አይደለም፡፡

ትችታቸውና ማብጠልጠላቸው የተበላሸውን ለማስተካል የፈሰሰውና ለማፈስ፤ የጎበጠውን ለማቅናት ሳይሆን የመቃወምና የማጠልሸት ሱሳቸውን ለመወጣት ነው፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እንደ ባህል የተያዘና ኢትዮጵያም በሰለጠነ መንገድ በሃሳብ ሙግት የፖለቲካ ስርዓት እንዳትገነባ እንቅፋት ሆኖባታል፡፡

በ21ኛው ክፍለ ዘመን በሥልጡን የፖለቲካ መንገድ ቢጓዙ የሚጠየቁት አንድ ነገር ብቻ ነው። እሱም የሕዝብን ቀልብ የሚስብ አጀንዳ ነው። ሕዝብ የሚፈልገው ሰላሙን በዘለቄታዊነት የሚያረጋግጥለት፣ ከድህነት አረንቋ ውስጥ የሚያወጣውና ነገን ብሩህ የሚያደርግለት ፖሊሲ ነው፡፡ ይህ ነው የሚባል አማራጭ ፖሊሲ ሳያቀርቡ መፎከር ዋጋ የለውም፡፡ አንዴ ቢሳካ እንኳ መድገም አይቻልም፡፡ ዘለቄታዊና አስተማማኝ የሆነ የሕዝብ ተቀባይነት ማግኘት የሚቻለው ግን ለውይይት፣ ለድርድርና ለመተማመን ዝግጁ የሆነ አደረጃጀትና ሥምሪት ሲኖር ነው፡፡ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ በዙሪያቸው ያሉ ወገኖች ከተራ ብሽሽቅ፣ እሰጥ አገባ፣ ሐሜት፣ አሉባልታና ለትዝብት ከሚዳርጉ ድርጊቶች መታቀብ ይኖርባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያን ታላቅ አገር አድርጎ በሰላም፣ በነፃነት፣ በፍትሕና በእኩልነት ለመኖር የሚያስችል ሥርዓት ዕውን ማድረግ የዘመኑ ትውልድ ኃላፊነት ነው፡፡

ይህንን ኋላ ቀር የፖለቲካ ምህዳር ለመለወጥ በርካታ ስራዎች ተከናውነዋል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት ተፈርጀው የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ፍረጃው ተነስቶላቸው በአገሪቱ የፖለቲካ መጫወቻ ሜዳ ላይ ተሠልፈዋል፡፡ ከእነዚህ ድርጅቶች መካከልም የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ)፣ አርበኞች ግንቦት ሰባት፣ እንዲሁም የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት) የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ሆኖም አንዳንዶቹ ቡድኖች አሁንም በድሮው መንገድ በመጓዝ በየጫካው ነፍጥ ማንሳቱንና መንግስትን በኃይል ለመቀየር ሲጣጣሩ እየተመለከትን ነው፡፡ ሆኖም ይህ የ1960ዎቹ አካሄድ ዘመኑን የሚዋጅ ካለመሆኑም ባሻገር ለሕዝብና ለሀገር ያለማሰብም ጭምር ነው፡፡

ኢትዮጵያ ከፊቷ የተጋረጡ በርካታ ችግሮች ያሉባት አገር ናት፡፡ የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሙሉ ለመነጋገርና ለመደማመጥ ጊዜ መስጠት አለባቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የጸጥታ ችግር አለ፡፡ ድርቅ፤ ጎርፍ፤ መፈናቀል በየጊዜው ይከሰታል፡፡ የኑሮ ውድነቱ እየባሰበት ነው። የወጣቱ ቁጥር በየጊዜው እያደገ ስለሚመጣ የሥራ አጥነቱ መጠን በፍጥነት እያሻቀበ ነው፡፡

ለዘመናት ሳይከፈሉ የቆዩ የአገሪቱ የዕዳ ጫና ከባድ ነው፡፡ ጥራት ያለው የትምህርትና የጤና አገልግሎት ተደራሽነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በገጠርም ሆነ በከተማ የሚኖሩ በርካታ ሚሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች ይኖራሉ፡፡ በሀገር ውስጥ ካለው አለመረጋጋትና ግጭት ባሻገር በተለያየ መልኩ የኢትዮጵያን ውድቀት የሚሹ የውጭ ጠላቶች እያደቡ ኢትዮጵያን ማድማታቸው አልቀረም፡፡

ስለዚህም በዚህ ወሳኝ ጊዜ ከግል ፍላጎት ወጥቶ በሰከነ መንገድ መነጋገርና መደማመጥ ያስፈልጋል። ፖለቲከኞች ምኅዳራቸው በሥርዓት ተመሥርቶ ሰላማዊ የፖለቲካ ፉክክር እንዲፈጠር፣ ልዩነቶቻቸውን አስታርቀው በጋራ መሥራት አለባቸው፡፡ በተለያዩ መስኮች የተሰማሩ ምሁራንና ልሂቃን ለፖሊሲዎች ግብዓት የሚሆኑ ድጋፎችን የማበርከት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ መንግሥት ግብዓቶችን ተቀብሎ ተግባራዊ እንዲያደርጋቸው ተደራጅተው ጫና ማሳደር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለአገራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችሉ ልምድ ያካበቱ ወገኖች በማሰባሰብ ጭምር አገራዊ ኃላፊነት መወጣት ግዴታቸው ነው፡፡ በተጨማሪም በአገሪቱ የመነጋገርና የመደማመጥ፣ እንዲሁም የመተማመን ባሕል እንዲጎለብት ግፊት ማድረግ አለባቸው፡፡

በሌላ በኩል ባሉት ችግሮች ላይ ተጨማሪ ችግሮች በመቀፍቀፍ ላይ የተጠመዱ ወገኖችም፣ አንድ ጉዳይ ላይ አጽንኦት ቢሰጡ መልካም ነው፡፡ የሚፈልጉትን ዓላማ ለማሳካት ሲነሱ፣ የሕዝብን ሕይወትና የአገርን ሕልውና አደጋ ውስጥ ከሚከት ድርጊት መታቀብ አለባቸው፡፡ በእነሱ ምክንያት ንፁኃን ሲገደሉ፣ ንብረታቸው ሲዘረፍና ሲወድም፣ ሲፈናቀሉና የአገር ሰላም ሲታወክ ለጊዜው ከሕግ ተጠያቂነት ቢያመልጡም፣ ከታሪክ ተጠያቂነት የሚታደጋቸው ግን የለም፡፡ ከሕግ ለጊዜው ቢሰወሩም ቆየት ብሎ ፍትሕ ደጃፍ ላይ መገተራቸውም አይቀሬ ይሆናል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን ግን ለሀገር እና ለሕዝብ ሰላም ሲባል የተጀመሩ የሰላም ጥረቶች ሁሉ መቀጠል አለባቸው። ሕዝብም ሰላም ወዳዱን እና ለሰላም ጀርባውን የሚሰጠውን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ነገ ከነገወዲያ ከሰላም ርቀው ግጭትና ሁከትን መተዳደሪያቸው ያደረጉትን እንዲሁም በሕዝብ ስም እየማሉ ሕዝብን የሚገሉ፤ የሚያቆስሉ፤ የሚያፈናቅሉና የሚያጎሳቁሉ ወገኖች በሕዝብ ክንድ የእጃቸውን ማግኘታቸው አይቀሬ ነው፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## “የሰው ገጽ” እፍታዎች

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**አትጠይቁኝ**

**የት አለሽ አትበሉኝ ድንገት ተነስታችሁ፤**
**ከተዋችሁኝ ስፍራ ከጣላችሁኝ ቦታ አጣናት ብላችሁ፤**
**የት ጠፋሽ አትበሉኝ ብዙ ጠብቃችሁ፤**
**ከትልቁ ስፍራ ከማማው ወጥቼ ስላልታየኋችሁ፤**
**በፊት ጅማሪዬን ዕቅድና ትልሜን አባሪ አድርጋችሁ፤**
**እንቅፋት፣እሾሁን፣ ምቹ፣ ሾተላዩ አልታይ ብሏችሁ ፤**
**ስለምን ዘገየሽ? የት ቀረሽ ? እያላችሁ፤**
**የተዳፈነውን የውስጤን ሽፍንፍን ትነካካላችሁ።**
**አለሁኝ አለሁኝ በቆምኩበት ስፍራ**
**ሁሉም ሳይቀርብኝ እያየሁ በተራ**
**ተቸገርኩኝ እንጂ በወይኑ እርሻዬ እሾህ እየፈራ።**

አንጠይቅም…ደግሞ ከወዴት እንዳለች ከማወቅም አንቆጠብም፡፡ ቅሉ እርሷ አትጠይቁኝ ብትለንም፤ ወዴት እንዳለች ግን ሳንጠይቅም ደርሰንበታል። ድሮስ ጥበበኛ ከወዴት ሊሆን ይችላል?… ከጥበብ መንደር፤ ከብዕር ዋርካ ጥላ ሥር ካልሆነ በቀር። ዳሩ የእርሷ መልዕክት፤ ከሰው ገጽ የምናብ ባሕር ውስጥ ሳለች ከሕይወቷ ግዙፍ መርከብ ላይ፤ በሀሳብ እያቃጨሉ እረፍትን ለነሷት የሀሳብ ተውሳኮች ቢሆንም፤ እኛ ግን ለኛም ይድረስ ብለን ከወዴት አለሽ ልንል የግድ ሆኗል። እንግዲህ ጥበብን ተከትለን እርሷን…እርሷንም ተከትለን “የሰው ገጽ”ን አግኝተናል። “የሰው ገጽ”ስ ምንድነው? በወፍ በረር…በረን በአውሎ ንፋሱ እንዳንሳፈፍ፤ በጠሊቁ ሰምጠንም በጊዜና አየር እጥረት የፊታችንን እንዳንተፋው ከሁለቱም መሐል ሆነን “የሰው ገጽ”ን ከእፍታ መሶብ ወርቁ ላይ ቆርሰን ልንቃመስ ያስመኘናል። የእፍታ ታህል ከምናነሳባት ከዚህቹ መሶብ ወርቅ ውስጥ፤ ለዛሬው ደርሶን ባናገኘውም ሌላ እንጎቻ ስለመኖሩም እንዳንዘነጋ፤ እኛም…ደራሲዋም ታስገነዝበናለች።

እንግዲህ ሰሞነኛ ጥበብ ማደሪያዋን ከወዲህ አድርጋለች፤ ከየት ካላችሁ ዘንድ…ካለችበትና ጥበብ ከተሰናዳችበት። ጥበብ ጥበብ ሲሸተን፤ የጥበብ የእግሯን ኮቴ፤ የጠረንዋን መዓዛ ተከትለን በስተመጨረሻም ከብሔራዊ ቲያትር አድርሳ አገናኘችን። እዚህ መከተሟ በምክንያት ነው። እሷን ፍለጋ ወጥቶ ከዚያ የተገኘውም አንድ ጉዳይ ሽቶ ነው። ጉዳዩም “አትጠይቁኝ” ስትል ከስንኞቿ ጋር በመግቢያችን የሞገተችን ደራሲና ጋዜጠኛ ፍሬዘር ዘውዴ፤ ሁለተኛውን የጥበብ ልጇን ወልዳለችና ‘እንኳን ጥበብ ማረችሽ’ ስንል የመጽሐፍ ልጇን ለመሳምና ከቀለም ጠብታ እንትፍ ብለን ለመመረቅ ነው። ደራሲና ጋዜጠኛ ፍሬዘር ዘውዴ፤ በብዙ የምናብ ምጥ ተጨንቃ የወለደችውን “የሰው ገጽ” የተሰኘውን የግጥም መጽሐፏን ከእንጎቻ ወጎች ጋር በእቅፍ አነባብራ፤ በጥበብ ታጅባ ከብሔራዊ ቲያትር መገኛዋን አድርጋለች። ምስጋና ለደራሲያን ማኅበር ይግባና በተንጣለለውና የጥበብ ናርዶስ በፈሰሰበት፤ በግዙፉ የብሔራዊ ቲያትር አዳራሽ ለመታረስም በቅታለች። የደራሲያን ማኅበርን ማንሳታችን፤ ደራሲዋ የዚህ ማኅበር አባል በመሆኗም ነው። እንግዲህ ማኅበሩም የልጅነት ፈቃድ ለሰጣቸው አባላቱ አለኝታነቱን ከሚያሳይባቸው ጉዳዮች መካከል አንደኛው፤ አባላቱ በሚከትቧቸው የመጽሐፍ ሥራዎች ውስጥ ከጎናቸው በመሆን ከግባቸው እንዲደርሱ ማድረግ ነው። ዛሬም ለደራሲዋ ደጀን ቆሞ ያማረውን ልጇን ባማረ መልኩ እንድታስመርቅ ሆኗል።

እንዲህ አይነት ማኅበራት በሁሉም ዓለማት የሚገኙ ቢሆንም፤ እንደ አፍሪካ ብሎም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ላሉ ደራሲያን ያለው ሚና አለ የማይባል ነው። የእጦት ችንካር በተቸነከረባቸው ሀገራት ውስጥ በምጥ የሚሞቱት እናቶች ብቻ ሳይሆኑ ጠቢባንም ጭምር ናቸው። ከማህፀን ምጥ የባሰው ምጥ፤ ምናባዊ የአዕምሮ ምጥ ነው። ላይገላገሉት እድሜ ዘመናቸውን ጥበብን በምናብ እያማጡ ኖረው እንዳማጡ ይሞታሉ። በእድልህ እደግ ተብሎ አይወለድ ነገር ጭንቅ ነው። ልጅ በድሉ፣ ሀብታሙ…ወዘተርፈ ተብሎ ስሙን መልአክ አያወጣለት ነገርም እዳ ነው። ብቻ ግን ከአፈር በላይ የሚውሉትን ዘለዓለማዊ የጥበብ ልጆቻቸውን ወልደው ስመው ለወግ ለማዕረጉ የሚያሳኩበትን ገንዘብ ከማጣት የተነሳ፤




**“የእናንተና የኛ አባቶች፤ እናትና አጎቶች እንዲሁም ዘመዶች…አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍሰው ይቺን የማትበገር ኢትዮጵያን ሰጥተውናል። እኛ ደግሞ የነገሩንና ያየነውን፤ የሰማነውንም እውነተኛ ታሪክ ለልጅ ልጆቻችን እናወርሳለን**

ሳይወልዱም ሳይስሙም፤ ቀና ያላለች ቀናቸው ደርሳ ከነምጣቸው ተፈግመው አፈር ይለብሳሉ። ስማቸውን በሥራዎቻቸው ለዘለዓለሙ ሕያው አድርገው ማኖር የሚችሉ ስንቶቹ መወለድ፤ መሞታቸውንም ሳናውቅ አፈር ታቅፈው ለአፈር ግብር ውለዋል። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ካለው አጭር እድሜና የቅርብ ጊዜ ታሪክ አንጻር በብዙ ሀገራት እንደምንመለከተው አይነት፤ እጁን በችሮታ ዘርግቶ ለአባላቱ ከኪሱ ገንዘብ ለመስጠት አልታደለም። ይልቁኑ ነብሱን የሚያቆየውም ከአባላቱ የሚሰበሰበውን ገንዘብ እየቀማመሰ መሆኑ ነው። በአሁኑ ሰዓትም ለአባላቱ ካለው ኃላፊነት መሐከል ዓበይቱ፤ ደራሲያኑ ያሰቡት ተሳክቶ፤ ሕልማቸው እውን ይሆን ዘንድ በሥራዎቻቸው ከጎናቸው በመቆም፤ አጋር ሊሆኑ የሚችሉ አካላትን ከመፈለግና ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ጀምሮ የአቅሙን ይጥራል። እንግዲህ አንድ ቀን ያጠረው እጁ እረዝሞ፤ ማድጋ ወጭቱ ሞልቶ፤ ከአቁማዳውም ተትረፍርፎ እንመለከተው ይሆናል በማለት በእፍታ እንለፈው።

ወደ ዋነኛው ርዕሰ ጉዳያችን እምብርት ሰትረን ከመግባታችን በፊት ጥቂት ስለ ደራሲዋ እንበል። ፍሬዘር ዘውዴ ውልደትና እድገት እዚሁ ከአዲስ አበባዋ ክንፍ ቀራኒዮ መድኃኒዓለም መንደር ውስጥ ነው። አዲስ ከተማ ትምህርት ቤት፤ በእውቀት የተለወሰውን የፊደል ማር የበላችበት፤ ሀሁ የቆጠረችበትና ዛሬም ድረስ ከትዝታዋ ማህደር ያልተፋቀ የሕይወት ብርሃን ያየችበት ነው። አብዝታም ስሙን መጥራት ትወዳለች። ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የእውቀት መንገድ ተዋውቃበታለች። ከልጅነቷ ጀምሮ በአንቀልባዋ አዝላ ያኖረችውን ሥነ ጽሑፍ፤ በተለይም የግጥም ፍቅሯ ከፍቅርነት አልፎ የመጀመሪያውን ፍሬዋን የተመለከተችውም በዚሁ በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ ነበር። ከዩኒቨርሲቲው የባሕልና የኪነት ቡድን አባላት ከነበሩ ጓደኞቿ ጋር በመጣመር የግጥም መድብል አሳትማለች። በሥራው ዓለም ሳለችም፤ በግሏ የመጀመሪያ የሆነውን “የፍቅር ገጽ” የተሰኘ የግጥም መድብል ለጥበብ አፍቃሪያኑ አቋድሳለች። ከ”የፍቅር ገጽ” የቀጠለው ሁለተኛው ሥራዋ ደግሞ ከሰሞኑ ለምርቃት የበቃው “የሰው ገጽ” የተሰኘው ይሄው ድንቅ የግጥም ሥራዋ ነው።

ኅዳር 15 ቀን ቀጠሮውን ቆርጦና ቆጥሮ በብሔራዊ ቲያትር ይህን ሊያስመለክት ከልበ ደጋጎቹ ዘንድ ደርሷል። ኪነ ጥበብ፤ የጥበብ ገብረዲኑን ለብሶ ካማረ ሸማው ጋር በፍቅር ከትሟል። ለጥበበኞች ጥበብን ለጀግኖቹም የክብርን ዘውድ ሊደፋ በግርማው ተገልጧል። ጠቢባን፣ የጥበብ አፍቃሪያን፤ እንዲሁም ጀነራል ካሳዬ ጨመዳን ጨምሮ የጦር ሜዳው ሊህቀ ህሩያን ከአዳራሹ ተንቆጥቁጠዋል። “እናንተ ልበ ጥሩዎች..እናንተ ደጋጎች… እናንተ መልከ መልካም የሀገሬ ልጆች..” በማለት ጀመረች፤ የመድረኩን የመግቢያ መጋረጃ የገለጠችው ደራሲና ጋዜጠኛ እንዲሁም በእለቱ በጥበብ ያጌጠችው የጥበብ ባለጸጋ፤ ፍሬዘር ዘውዴ…ጸጋዋ የሥነ ጽሑፍ ብቻም አይመስልም፤ ብዙዎቻችን የጎደለንን የአመስጋኝነትን ጸጋም የተቸረች ትመስላለች። የምስጋናን ማር ካንደበቷ ታፈልቃለች። ለኛ የዛሬ ማንነት መሻገሪያ ድልድይ የሆኑትን በሕይወት ሳሉ የሚገባቸውን ሳንሰጥ፤ ከሞት ወዲያ መገነዣ ከፈን አድርገን ብናቀርበው ለሄደው ከሞት አንቂ ስሜት አይሰጠውም። ሀገርና ሕዝቧን የምትወድ፤ በእናትና አባቶቻችን ወግና ሥርዓት ተቀርጻ ያደገች ስለመሆኗ የእለቱ ዝግጅት ፍንትው አድርጎ ለማሳየትም ይዳክራል።

“የሰው ገጽ” የተሰኘው መጽሐፍ ግጥሞችን ብቻም ሳይሆን እንጎቻ ወጎችንም አካቶ የያዘ ነው። በግጥሙ፤ ስብጥር ስሜቶች እና እሱና እሷ የሚሉ ክፍሎች አሉት። እሱና እሷ እውነተኛ የታሪክ ቅምሻዎች ስለመሆናቸው ደራሲዋ ትናገራለች። በዚህም 5 አጫጭር ታሪኮች ተካተውበታል። “የሰው ልጅ ልክ እንደ ሸንኩርት የተለያየ ንብብር ስሜት፣ ማንነት፣ እውነት እና አመለካከትን የያዘ ደግሞም እያንዳንዱ ንብብር በተነሳ ቁጥር ሌላ ከቀደመው ተቃራኒ የሆነ አዲስ ገጽ የሚገኝበት ነው፡፡ ይሄ በሸንኩርት ገላ የተመሰለው ማንነት ግን፤ ልክ ሸንኩርት እያንዳንዱ ንብብር በተነሳ ቁጥር እየኮሰሰ ከዛም እንደሚያልቀው ሳይሆን ዘመን እስከፈቀደ ዝም ብሎ የሚገለጥ የማያልቅ ንብርብር ነው፡፡ እናም በዚህ መጽሐፌ እጅግ በጣም ጥቂት የሰው ገጾች ቀርበዋልና እርስዎም ይግለጧቸው…” ትለናለች። ፍቃዷ ሆኖ ግለጡት ካለችን ዘንድ፤ እኛም ይሄን የሰው ገጽ ገልጠን ወርቁንም፤ ሰሙንም…ቅኔውንም ሆነ ግጥሙን ለመመልከት አይሰለቸንም፡፡ በጥበብ መታቀፊያ እያኖርን ዳግም እንኳን ጥበብ ማረችሽ እያልን ስመን ለመመረቅ እንወዳለን።

“የሰው ገጽ” ሰው የመሆንን ሚስጥር፤ ከሰውም ኢትዮጵያዊ የመሆንን ምስጢር በስንኞች እየቋጠረ መልክና ወዘናውን እጹብ ድንቅ ጣዕሙን ያጠግበናል። ግን…ሰው ማለት ምንድነው? የሰው ገጽስ? ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትስ… ማናቸው? ቅኔ ፍጡር…ቅኔ ሀገር…ቅኔ ሕዝብ ሁሉም በግጥም ቅኔ ውስጥ ተቃኝተዋል። ደራሲዋ ፍሬዘር ዘውዴ፤በዚህ “የሰው ገጽ” በተሰኘው በሁለተኛው ልጇ ውስጥ ሁሉንም ለማየት ታትራበታለች። “ግጥም እኮ ማብራሪያ አይሻም። ምክንያቱም ግጥም ጥያቄ እንጂ ምላሽ አይደለም። ግጥም ትንቢት ተናጋሪ እንጂ ሁነትን አብራሪ አይደለም” በማለት የዚህ መጽሐፍ አርታኢ የነበሩት መምህር መሠረት አበጀ፤ የግጥምን ገጽ ገልጠው ለማሳየት ሲሞክሩም ሰምተን ነበር። እውነት ነው፡፡ የሰው ልጅ ገጽና የግጥም መጋረጃ፤ ውስጡ በማብራሪያ የሚገለጥ አይደለም። ግጥምም ለአይን የቀረበ የቅኔ ወሰን የለውም። የሰው ልጅም የማንነትና የምንነት መለኪያ ቁና የለውም። የግጥም ቅኔ ጥልቀትና የሰው ልጅ ገጽ ስንት ነው ተብሎ ተቆጥሮ አይደረስበትም። ነጭ ሲሉት ጥቁር፤ ቢጫ ሲሉት ግራጫ፤ መልአክ ሲሉት ሰይጣን፤ ሲኦል ሲሉት ገነት ነው። “የሰው ገጽ” ደራሲዋ ጥላቻና ፍቅርን፣ እውነትና ውሸትን፤ ትላንትናና ዛሬን እንዲሁም ሀገርና ሕዝብን በሰው ልጅ ገጽ ውስጥ እየሾረች፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱ የግጥምና የወግ ሥራዎች ውስጥ ለመደወር ሞክራለች።

የኅዳር 15ቱ የብሔራዊ ቲያትር የረፋድ ቆይታ ሀገር ሀገር እንዲሸት ካደረጉት ነገሮች አንደኛው፤ በምስጋና የታጀበው የሀገር ባለውለታ ጀግኖች የእውቅና አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት ዋነኛው ነበር። በዚህ መሠረትም ይህቺን ሀገር ከትውልድ እስከትውልድ ጠብቀው ያስረከቡን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ግንባር ቀደሙ ነው። ማኅበሩ ዛሬ ላይ ለዛሬ የተመሠረተ ሳይሆን ፋሽስቱ ድባቅ የተመታበትን ጊዜ መነሻውን በማድረግ በትውልድ ሐረግ ሽቅብ እየተምዘገዘገ ዛሬና ዘንድሮን ደርሷል። እኚያ ታላላቅ አባቶች እኛን ከአፈር በላይ አኑሮው እነርሱ ግን ከአፈር በታች ናቸው። ይህ ማኅበር ዛሬ ብዙ የጦር ሜዳ ጀግኖችን ያቀፈ ቢሆንም፤ በብዛት ግን ለዚሁ ቅርብ በሆኑ በአርበኛ ልጆችና የልጅ ልጆች ጭምር የቆመ ነው። “የእናንተና የኛ አባቶች፤ እናትና አጎቶች እንዲሁም ዘመዶች… አጥንታቸውን ከስክሰው፤ ደማቸውን አፍሰው ይቺን የማትበገር ኢትዮጵያን ሰጥተውናል። እኛ ደግሞ የነገሩንና ያየነውን፤ የሰማነውንም እውነተኛ ታሪክ ለልጅ ልጆቻችን እናወርሳለን። የኛ ማኅበር ዛሬ ላይ ልክ እንደቀደምቶቻችን ሁሉ በጦር አውድማ ላይ ባይጋደልም፤ ተጋድሎው ከታሪክ ጋር ነው። በአንዳንድ አላዋቂዎች ምክንያት እየተበረዘ ያለውን ታሪካችንን በማንጻት እውነተኛዋን ኢትዮጵያን እንድንመለከታት ለማድረግ ይሠራል” ሲሉም የማኅበሩ ፕሬዚዳንት የሆኑት ልጅ ዳንኤል መስፍን(ጆቴ) የእውቅናና የምስጋና ሰርተፊኬታቸውን በተቀበሉበት ጊዜ ተናግረዋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ለአበርክቶው እውቅና የተበረከተለት ሌላኛው ደግሞ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጽሐፍት አገልግሎት(ወመዘክር) ነበር። በእርግጥም ተቋሙ እውቅናም ሆነ ሽልማት የሚያንስበት እንጂ የሚበዛበት አይደለም። ዓላማው ትውልድን በእውቀት መቅረጽና በጽሑፍ የሠፈሩ የሀገር ሀብትና ንብረቶችንም መጠበቅ ነው። ተቋሙ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ በዩኔስኮ ያስመዘገበቻቸውን 12 የሥነ ጽሑፍ ሥራዎችን እንዲሁም በርካታ የሆኑ የጥንት መጽሐፍት፣ አዲስ ዘመንን ጨምሮ ቀደም ሲል የነበሩ ጋዜጦች፣ መነን መጽሔትና ሌሎች ጎልቁ መሳፍርት ጽሑፎችን አካቶ ይዟል። ከዚህ ባሻገርም የንባብ ባሕል ይዳብር ዘንድ በየሳምንቱ በሀገራችን ልዩ ልዩ ክፍሎች የንባብ ሳምንትንም ያዘጋጃል።

እንግዲህ እፍታ… ኩሬና ባሕር፤ ትንሽና ትልቅ የለውምና ካየንና ከሰማነው ብዙ ነገር፤ ያወቅነውንና የተረዳነውን ጥቂት ነገር እንዲህ ባለ መልኩ አወሳናችሁ። ከጥበብ ባሕር እየቀዳች፤ ከሰው ገጽ ባሕሪ እየጨለፈች፤ ከፍቅር ሸማ እየፈተለች “የሰው ገጽ” የተሰኘውን የግጥም መድብሏን የደወረችው ደራሲና ጋዜጠኛ ፍሬዘር ዘውዴ፤ ከምናባዊው ፀአዳማ ሰማይ፤ ከምድራዊው የገነት ልምላሜ፤ ነፋሻማውን አየር ለመኮምኮም እየተመኘች፤ በመጨረሻም በስንኞቿ እንዲህ ትላለች።

**ና ኮከብ እንቁጠር!**

**ና ኮከብ እንቁጠር በጭፍን ሰማይ ላይ፤**
**ባዶ በሚመስለው ከደመናው በላይ፤**
**ኮከብ አልባ የሆነ ከጥቅል ጢስ መሳይ፤**
**ጨረቃን ካፈነ የጉም ጥቅጥቅ ፍታይ፡፡**
**ምንም ከሌለበት እንዳልነበር ሆኖ፤**
**ክዋክብት እንቁጠር እኛ በተቃርኖ፡፡**
**በዚህ አይነት ምሽት በእንዲህ አይነት ሰማይ፤**
**ጨረቃና ኮከብ ለእኛ ብቻ እንዲታይ፤**
**ልባችን ሰሌዳ እንዲወክል ሰማይ፤**
**አይናችን ከኮከብ ደምቆ አምሮ እንዲታይ፡፡**
**ሁሉን የፈጠረ በሩህያችን ፅፎ፤**
**ያኖረ ይመስለኛል ጊዜን አስደግፎ፡፡**
**ና ኮከብ እንቁጠር በጭፍን ሰማይ ላይ፤**
**ሁሉ ተቀምጧል ለእኛ ብቻ እንዲታይ፡፡**

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ሽልማቱን እንደማነቃቂያ

እየሩስ ተስፋዬ

መምህር ያደታ ኢማና በመድኃኒዓለም ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት መምህር ናቸው፡፡ ለ35 ዓመታት በመምህርነት ሙያ አገልግለዋል። መምህሩ ለሦስት ዓመታት ብቻ ነበር ጉዳት ሳይደርስባቸው ተማሪዎች ያስተማሩት። በጊዜ ሂደት ግን የአጥንት ካንሰር በሽታ አጋጠማቸው። በጠና ታመው ለሁለት ወራት ያህል በሆስፒታል አሳለፉ። ሕክምናቸውን ጨርሰው ከወጡ በኋላ ለስድስት ወራት ያህል በክራንች መሄድ ግድ ሆነባቸው፡፡ እግራቸው ቢያስነክሳቸውም ያለ ክራንች ድጋፍ በመንቀሳቀስ ዛሬም ትውልድን በመቅረጽ የመምህርነቱን ሙያ ገፍተውበታል፡፡

በኢትዮጵያ በብዙ ዘርፎች የተለያዩ ሽልማቶች ሲሰጡ የተመለከተው የካቲም አካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ እና ድጋፍ ድርጅት መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ ወጣት አማኑኤል ሰለሞን እንደሚለው፣ አካል ጉዳተኞች ላይ ያለው ጫና የበረታ ነው። ጫናዎችን ተቋቁመው ውጤታማ የሆኑ ተማሪዎች ተምረው ቢመረቁ ሥራ አንይዝም የሚል አመለካከት ስላላቸው እንዲህ አይነቱን ሽልማት በመስጠት ለማበረታት ያለመ ነው። ይህንን እነርሱ ይጀምሩት እንጂ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮም ሆነ የትምህርት ሚኒስቴር ሥራውን በባለቤትነት እንዲቀጥሉት ይፈልጋሉ፡፡

እንዲሁም አካል ጉዳተኛ መምህራን በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው ምቹ እና ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ እንዲሁም ሀገር የምትኮራባቸው ተማሪዎችን ያፈሩ ብዙ መምህራን አሉ፡፡ እነዚህ መምህራን ታዲያ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መሆናቸውን በመረዳት፤ መምህራኑን ለማመስገን እንዲሁም ክብር በመስጠት ተስፋ እንዳይቆርጡ ለማበረታታት ያለመ የእውቅና እና የሽልማት መርሐ ግብር ኅዳር 17 ቀን 2016 ዓ.ም በብሔራዊ ቴአትር ተካሂዷል፡፡

ሽልማት ካገኙት መካከል አብዛኞቹ ከ28 ዓመት በላይ በመምህርነት ያገለገሉ ሲሆን፤ እነርሱን ማበረታታት ክብር መስጠት እና መሸለም «ለካ የሚመለከተን አካል አለ» ብለው ተስፋ ሳይቆርጡ እንዲሠሩ ከማድረግ በሻገር ምርታማ የሆኑ ተማሪዎችን ለማፍራት ስንቅ ይሆናቸዋል፡፡

አቢጊያ ውብአለ ደግሞ የእድገት ጮራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ናት፡፡ በከፊል የእይታ ችግር አለባት፡፡ እርሷም ሽልማቱን ከተቀዳጁት 12 ተማሪዎች መካከል አንዷ ናት፡፡ የ10ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን፤ በ2015 ዓ.ም ከክፍሏ አንደኛ በመውጣት ለሽልማት በቅታለች፡፡



የካቲም የዳንስ ቡድን አባላት፣

«ሴትነቴን በጣም እወደዋለሁ፡፡ ለወደፊት የተገደበች ሴት መሆን አልፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ከረዳኝ በቀጣይ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሴት ለመሆን እፈልጋለሁ፡፡ በተጨማሪም ሕግ እና ሕክምና ባጠና ደስ ይለኛል፡፡» በማለት የወደፊት ሕልሟን ገልጻለች፡፡ አካል ጉዳተኛ መምህራን እና ተማሪዎች እንዲህ መሸለማቸው ደስ የሚል እና የሚበረታታ እንደሆነ የምትገልፀው ተማሪ አቢጊያ፤ እርሷም ለወደፊት አካል ጉዳተኞችን የሚያበረታቱ እና የሚያግዙ ሥራዎችን ለመሥራት ፍላጎት እንዳላት ታስረዳለች፡፡

ከ28 ዓመታት በላይ በመምህርነት አገልግለው ሽልማት ከተሰጣቸው መምህራን መካከል ተጠቃሽ የሆኑት የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር ያደታ ሽልማቱ የሚያበረታታ መሆኑን ይናገራሉ። እንዲህ ዓይነቱ ሽልማት ቀጣይነት ያለው መሆን ይኖርበታልም ባይ ናቸው፡፡ ሌሎች አካል ጉዳተኞችን ለማነቃቃት ይጠቅማልና፡፡

የካቲም አምባሳደር የሆኑት አምባሳደር ሙሉ ሰለሞን በበኩላቸው፤ «አካል ጉዳተኝነት ሲባል ብዙዎቻችን የተገደበ ነገር ነው ብለን ነው የምናስበው፡፡ ነገር ግን አካል ጉዳተኝነት ገደብን ማንሳት ነው፡፡» ሲሉ ጀግናና ምሳሌ ሆነው ለሽልማት ለበቁት መምህራን እንዲሁም ተማሪዎች ያላቸውን ድጋፍ ገልጸዋል፡፡

ወጣት አማኑኤል እንደሚናገረው የአካል ጉዳተኝነት ተግዳሮቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ «የዚህን ዓመት ጥርሳችንን ነክሰን ነው ያዘጋጀነው፣ የሚያግዘን አካል የለም፡፡» ይላል ስለሽልማቱም ሲያስረዳ፡፡ «እንችላለን» የሚለው በየዓመቱ የሚዘጋጀው መርሐ ግብር እንዲቀጥልም ይፈልጋል። ትኩረት አድርገው የሚሠሩት ኪነጥበብ ላይ ነው። ለኅብረተሰቡ አካል ጉዳተኞች መሥራት እንደሚችሉ በማሳየት መንግሥት እንዲቀጥልበት ከማድረግ በሻገር መገናኛ ብዙኃንም ትኩረት ተሰጥተው መሥራት አለባቸውም ይላል ፡፡

እንደ መሥራቹ ወጣት አማኑኤል ገለፃ ዝግጅቱ በተጠበቀው ልክ አይደለም፡፡ መገናኛ ብዙኃን እንዲህ አይነቱ ዝግጅት ላይ ተሳትፏቸው አናሳ ነው፡፡ ዛሬም ቢሆን በየቤታቸው የተደበቁ ብዙ አካል ጉዳተኞች አሉ። አካል ጉዳተኛ ወላጆች ያሏቸው ብዙ ልጆች አሉ፡፡ አካል ጉዳተኛ ልጅን በሰንሰለት አስሮ ማስቀመጥ፤ እንግዳ ሲመጣ ልጁን የሚያሸሹ ብሎም የሚደብቁ ብዙ ሰዎች ናቸው። ስለዚህም ሰዎች ግንዛቤ እንዲያገኙ መገናኛ ብዙኃን ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የአካቶ ትምህርት ወይም ድጋፍ የሚያሻቸው ተማሪዎች በቂውን ትኩረት እያገኙ አይደለም የሚሉት መምህር ያደታ፤ የማየት ፣ የመስማት፣ ግልፅ ያልሆነ እና ሌሎች ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች መኖራቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሀገሪቱ አካል ጉዳተኞችን ብትደግፍ ከዚህ የበለጠ እድገት ልታስመዘግብ ትችላለች፡፡ ትኩረት ማድረግ የሚገባው አካል ጉዳቱ ላይ ሳይሆን ችሎታው ላይ መሆን አለበት፡፡

ወጣት አማኑኤል እንደሚናገረው፣ አሁን ላይ በኢትዮጵያ ከ20 ሚሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች አሉ። ቁጥሩ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለዚህም ይህንን ከፍተኛ ቁጥር ዘንግቶ ምንም ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ብዙ ውጤታማ መሆን የሚችሉ ተማሪዎች ጓዳ ቢቀመጡ ወይም ወደ ሱስ ቢሄዱ ሀገሪቷ ትጎዳለች፡፡ ምርታማ ዜጋ ለማፍራትም አዳጋች ይሆንባታል። ይህን ከፍተኛ ቁጥር ወደ ምርታማነት ቢቀየር ሀገር በሚገባ ትቀየራለች፡፡

ቴአትር ቤቶች አካል ጉዳተኛ ሲቀጥሩ አይታይም። ለአካል ጉዳተኛ ተብሎ የተመረጠ ሥራ አለ፡፡ የኪነጥበብ ዘርፍ የተተወው ለሌላ ይመስላል፡፡ በትምህርት ቤቶች አካል ጉዳተኞች እንቅስቃሴ የተገደበ ነው፡፡ ቡድኑ ይህንን ችግር ለመፍታት በአሁን ወቅት በስምንት ትምህርት ቤቶች ለዓይነ ስውራን፣ መስማት ለተሳናቸው እና የአእምሮ እድገት ውስንነት ላለባቸው ተማሪዎች የአካል ብቃት እንቅስቃሴ እየሰጠ ይገኛል፡፡ በቀጣይ ይህንን ሥራ አጠናክሮ ለመሥራት ታስቧል፡፡

አሁን ላይ በርካታ ፈተናዎች አሉ፡፡ አካል ጉዳተኝነት እንደ ጥላ የሚከተል በተጨማሪም ማንም ሰው ነገ ላይ ጉዳተኛ ላለመሆኑ ዋስትና የለውም፡፡ በመሆኑም መንግሥትም ይሁን ሌሎች ደጋፊ አካላት የአካል ጉዳተኛውን ሕይወት ሊቀይር የሚችል ሥራዎች ማበረታታት ይገባል፡፡ የአካል ጉዳተኞች ቀን ብሎ ከመዘከር ባለፈ ተግባራዊ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

# ዓለም አቀፍ



## የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን በጃፓን መከስከሱ ተገለጸ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን በጃፓን መከስከሱ ተገለጸ፡፡

የዓለማችን ልዕለ ኃያል የሆነችው አሜሪካ በተለያዩ ሀገራት የጦር ሰፈር ያላት ሲሆን ከነዚህ መካከልም ጃፓን አንዷ ናት፡፡

በደቡባዊ ጃፓን ባሕር ላይ ቅኝት ሲያደርግ የነበረ የጦር አውሮፕላን እንደተከሰከሰ ኤ.ኤፍ.ፒ ዘግቧል፡፡

እንደዘገባው ከሆነ ይህ አውሮፕላን ስምንት ሰዎችን አሳፍሮ ነበር የተባለ ሲሆን በአውሮፕላኑ ላይ የነበሩ ሰዎች ደህንነትን የተመለከቱ መረጃዎች እስካሁን ይፋ አልተደረገም።

ፔንታጎን በጃፓን ስለተፈጠረው ክስተት እስካሁን የተጎጂዎችን ማንነት፣ የአደጋው መንስኤ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን ይፋ ከማድረግ መቆጠቡም ተገልጿል።

ባሳለፈነው ነሐሴ ወር ላይ በአውስትራሊያ በልምምድ ላይ የነበረ የአሜሪካ የጦር አውሮፕላን ተከስክሶ በውስጡ የነበሩ ሁሉም ወታደሮች ሕይወት ማለፉ ይታወሳል፡፡

እንዲሁም ባሳለፍነው ግንቦት ወር ላይ ኤፍ 16 የተሰኘው የውጊያ አውሮፕላን በደቡብ ኮሪያ ኦሳን አውሮፕላን ማዘዣ አቅራቢያ ተከስክሷል መባሉ አይዘነጋም።

የአውሮፕላኑ አብራሪን ከከፋ ጉዳት መታደግ የተቻለ ሲሆን በአደጋው ሌሎች ንጹሐን ሰዎች ላይ ያደረሰው ጉዳት እንደሌለ ሲኤን ኤን በወቅቱ ዘግቧል።

አውሮፕላኑ ከሰሜን ኮሪያ ሊሰነዘር የሚችልን ጥቃት በኮሪያ ባሕረ ሰላጤ ቅኝት በማድረግ ላይ እያለ እንደተከሰከሰ ተገልጿል።

## የዓለም ጤና ድርጅት በጋዛ ወረርሽኝ በርካታ ሰዎችን ሊጨርስ ይችላል አለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በጋዛ እየተስፋፋ የመጣው ወረርሽኝ ከእስራኤል የቦምብ ጥቃት በበለጠ የበርካቶችን ሕይወት ሊቀጥፍ እንደሚችል የዓለም ጤና ድርጅት አሳስቧል።

ተቅማጥ እና የመተንፈሻ አካላት ሕመም ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ፍልስጤማውያን ተጨናንቀው በሚኖሩባቸው የመንግሥታቱ ድርጅት መጠለያዎች በፍጥነት እየተዛመተ መሆኑንም ጠቅሷል።

የአምስት ዓመት እና ከዚያ በላይ ሕጻናት ላይ የበረታው የተቅማጥ ወረርሽኝ በኅዳር ወር መጀመሪያ ከነበረበት በ100 እጥፍ ጨምሯል ነው ያሉት የድርጅቱ ቃል አቀባይ ዶክተር ማርጋሬት ሃሪስ።

ሕጻናቱ ምንም አይነት ሕክምና እያገኙ ባለመሆኑም በአጭር ጊዜ ሕይወታቸውን ልናጣ እንችላለን ሲሉ አስጠንቅቀዋል።

እንደ መንግሥታቱ ድርጅት መረጃ እስራኤል የምድር ውጊያ ስታደርግበት በቆየችበት ሰሜናዊ ጋዛ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት አምስት ሆስፒታሎች ብቻ ናቸው።

ከነዚህ ሆስፒታሎች ውስጥ የቀዶ ጥገና ሕክምና እና ሌሎች ከባድ ሕመሞችን ማከም የሚችለው አንድ ሆስፒታል ብቻ ነው።

ለሆስፒታሎቹ ፈጣን ድጋፍ ተደርጎ ወደ ሥራ ካልገቡ ከእስራኤል የቦምብ ጥቃት የበለጠ ወረርሽኞች የበርካቶችን ሕይወት ይቀጥፋሉ ነው ያሉት የዓለም ጤና ድርጅት ቃል አቀባይ።

የዩኒሴፍ ቃል አቀባይ ጀምስ ኢልደር በጋዛ ባደረጉት ምልከታ ሆስፒታሎች በሕጻናት እና በጦርነቱ በቆሰሉ ሰዎች መጨናነቃቸውን ገልጸዋል።

የዓለም ጤና ድርጅትም ሆነ ዩኒሴፍ በዚህ ፈታኝ ወቅት ዳግም ጦርነቱን መጀመር የማይታሰብ ነው



ብለዋል፤ ዘላቂ የተኩስ አቁም ስምምነት ካልተፈረመ እጅግ የከበደ ቀውስ ይከሰታል ሲሉም አሳስበዋል።

የእስራኤሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ግን "ግባችን ለማሳካት ሙሉ አቅማችን እንጠቀማለን" በማለት ስምምነቱ ሲጠናቀቅ ጦርነቱ ዳግም እንደሚጀመር ተናግረዋል።

እስራኤልና ሃማስን አደራድራ የተኩስ አቁም ስምምነት እንዲደርሱ ያደረገችው ኳታር በበኩሏ ዘላቂ የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ እንዲደረስ ጥረት ማድረግ መቀጠሏን አስታውቃለች ሲል የዘገበው አል ዓይን ነው።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሺ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፡- በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፡- በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፡- በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፡ - የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፡- በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ሰው ሰራሽ...

ከ ገጽ 5 የዞረ

የዋሉበት ነው። ብዙ ሊቃውንት አሁን የምንገኝበትን ጊዜ የአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረበት፤ የዲጂታል ቴክኖሎጂ የተቀናጀበት፣ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ወደ ስራ የገባበት፣ በይነ መረብ እያንዳንዱን የሕይወት ቅንጣትና የኢኮኖሚ ዘርፍ ማዳረስ የጀመረበት ከመሆኑ ባሻገር በአኗኗራችንና በግንኙነታችን ላይ የዝሆን ዳናውን እየተው ያለ ምዕራፍ ነው። እጃችን የገባን ቴክኖሎጂ ተለማምደነውና ተዋውቀነው ሳናበቃ እጃችን ላይ የሚያረጅበትና በፍጥነት የሚለዋወጥበት ዘመን ነው።

ለብዙዎቻችን የሰው ሰራሽ አስተውሎት አዲስ ግኝትና ቴክኖሎጂያዊ እመርታ የቅርብ ጊዜ ክስተት ቢመስለንም የዘርፉ ልሒቃን ግን ጥንስሱ ጥንታዊ ነው ሲሉ ሀተታ ተፈጥሮንና ስነ ቃልን በዋቢነት ያወሳሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተስፋም ስጋትም ይዞ ወደፊት እየመጣ ያለው ሰው ሰራሽ አስተውሎት ግን የተጀመረው በ20ኛው መክዘ አጋማሽ ሲሆን የኮምፒውተር ሊቃውንት ስልተ ቀመር ወይም አልጎሪዝምና አስበው የሚሰሩ ማሽኖች ወደ ስራ እየገቡበት ያለ ጊዜ ነው።

በ1943 ዓ.ም ዋረን ማክኩሎችና ዋልተር ፒትስ በጋራ በነርቭ አውታረ መረብ የሚታገዝ ሒሳባዊ ሞዴል ወይም mathematical model of neural መፍጠራቸው ለዛሬው ሰው ሰራሽ አስተውሎት እርሾ ሆኖ አገልግሏል። በ1950 ዓ.ም አለን ተርኒግ እንደ ሰው ማሰብ የሚችል ማሽን ፈልስፎ ሙከራ አደረገ። በ1950ዎቹና 60ዎቹ General Problem Solver (GPS) እና ሎጂክ ቴዎሪስትን ጨምሮ በርከት ያሉ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ፕሮግራሞች በለጸጉ።

በ1956 ዓም የዳርትማውዝ ጉባኤ"ሰውሰራሽ አስተውሎት"ራሱን ችሎ እንዲጠና ከመወሰኑ ባሻገር ዛሬ የምንጠቀምበትን ይሄን መጠሪያውን አገኘ ። በዚሁ ጉባኤ የተሳተፉ የዘርፉ ሊቃውንት AI ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት አቅም እንዳለው ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ አደረጉ። በ1970ዎቹና 80ዎቹ በAI (Artificial Intelligence) ዘርፍ የሰውን ልጅ የመወሰን አቅም የሚተካከል የኮምፒውተር ፕሮግራምለማበልጸግ ርብርብ ይደረግ ነበር።

ዳሩ ግን በ1990ዎቹ የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ ባለመሆኑ ምርምሮቹ መቀዛቀዝ ጀምረው ነበር ። በ21ኛው መክዘ ደግሞ እንደገና ማንሰራራት ጀመረ። ከዚህ በኋላ ነጮች እንደሚሉት የተቀረው ታሪክ ነው ። ሰውን ተክተው የሚሰሩ፣ ስልተ ቀመርን algorithm የሚረዱ ማሽኖች ስራ ላይ መዋል ጀመሩ። በርካታ መረጃዎችን አብላልተው የሚሰሩ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ኮምፒውተሮች ወደ ስራ መግባታቸው ዘርፉን ያጎለብተው ጀመር።

አሁን አሁን AI የማይገባበት የሕይወት ቅንጣት የለም። በጤናችን፣ በማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችን፣ በመረጃ አፈላለጋችን፣ በፖለቲካችን፣ በትምህርታችን፣ በኢኮኖሚያችን፣ በምርምራችን፣ በግብርናችን፣ በማዕድን ፍለጋና ልማታችን፣ በአገልግሎት አሰጣጣችን፣ ወዘተረፈ እሱ በዚያ አለ። ለሰው ልጅ በርካታ ትሩፋት ይዞ የመጣ ቢሆንም ስጋት መደቀኑ አልቀረም።

የሰው ሰራሽ ክሕሎት በዚህ ከቀጠለና ያለ ሰዎች ጣልቃ ገብነትና ተሳትፎ ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ ከጀመረ የሰውን ልጅ ከምድረ ገጽ ሊያጠፋ ይችላል የሚል ስጋት እየፈጠረ ነው። የArtficial Intelligence AI ጉዳይ ብርቱ ጥንቃቄ ይጠይቃል ይሉናል በጎግል የሰው ሰራሽ ክሕሎት ቤተ ሙከራ የዲፕማይንድ ዋና ስራ አስፈጻሚ ዴሚስ ሀሳቢስ። ብዙዎቹ በAI ላይ ሙከራ እያደረጉ ያሉ ተመራማሪዎች እጃቸው ውስጥ የገባው ቴክኖሎጂ እጅግ አደገኛ መሆኑን በቅጡ የተገነዘቡ አይመስሉም ይላሉ ዋና ስራ አስፈጻሚው። በዘረ አዳም ሕልውና ላይ አደጋ ስለደቀነው የሰው ሰራሽ አስተውሎት ከተለያዩ ምንጮች ያጠናቀርሁትን መረጃ እንዲህ ላጋራችሁ ወደድሁ።

Artficial Intelligence ወይም AI ግስጋሴ በሰው ልጆች ሕልውና ላይ የደቀነው አደጋ፤ ከፉኛ ያሳሰባቸውና ያስጨነቃቸው ተጽዕኖ ፈጣሪዎች ለ6 ወር እንዲቆም በግልጽ ደብዳቤ መጠየቃቸው የዚያ ሰሞን መነጋገሪ ነበር። ኤለን መስክን ጨምሮ የAI አባቶች በመባል የሚታወቁ ከ1100 በላይ የዘርፉ ጉምቱ ሊቃውንት በፉክክርና በውድድር፤ እየተለቀቁ ያሉ የAI ግኝቶች በዚሁ ከቀጠሉ በሰብአዊ ፍጡር ላይ አደጋ ሊደቅኑ ስለሚችሉ እንዲቆሙ መንግስትንም ኩባንዎችንም ተማጽነዋል።

ተማጽኖው የመጣው ጉግልና ማይክሮሶፍት ራሱን ችሎ የሚሰራ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ከለቀቁ በኋላ ነው ይለናል የእንግሊዙ ዜና አገልግሎት ሮይተርስ። በግልጽ ደብዳቤ እንዲቆም ከጠየቁት መካከል የStability AI ዋና ስራ አስፈጻሚ ኤማድ ሞስታ፤ ዮሹዋ ቤንጊዎ፣ ስቱዋርት ሩሶ፣ የአፕል መስራች ስቲቭ ወዚናክ ሌሎች ኢንዱስትሪው ላይ የሚሰሩ ጉምቱዎች፤ ሰው ሰራሽ አስተውሎት ፈጣሪዎቹን ጨምሮ ማንም ሊቆጣጠረው፣ ሊረዳውና ሊተነብየው የማይችል አደጋ በሰው ዘር ላይ ስለደቀነ እንዲቆም ተማጽነዋል። ሲቆም ደግሞ የዘርፉን ተዋናዮችን ያሳተፈ፣ ለሕዝብ ግልጽ የሚሆንና ክትትል የሚደረግበት ሊሆን ይገባል ሲሉ ያስጠነቅቃሉ።

ፈጠራ ሰዋዊ ነው። የሰው ልጅ ላለፉት

በ1956 ዓም የዳርትማውዝ ጉባኤ"ሰውሰራሽ አስተውሎት"ራሱን ችሎ እንዲጠና ከመወሰኑ ባሻገር ዛሬ የምንጠቀምበትን ይሄን መጠሪያውን አገኘ ። በዚሁ ጉባኤ የተሳተፉ የዘርፉ ሊቃውንት AI ውስብስብ ችግሮችን የመፍታት አቅም እንዳለው ለመጀመሪያ ጊዜ ይፋ አደረጉ። በ1970ዎቹና 80ዎቹ በAI (Arti›cial Intelligence) ዘርፍ የሰውን ልጅ የመወሰን አቅም የሚተካከል የኮምፒውተር ፕሮግራምለማበልጸግ ርብርብ ይደረግ ነበር

300,000 ዓመታት ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ ኪነ ጥበባዊ ስራዎችን፣ የምግብ አሰራር ዘዴዎችን፣ የፖለቲካ ማኒፌስቶዎችን፣ ማሕበረሰቦችን፤ ባጠቃላይ ያልነበሩ አዳዲስ ነገሮችን ፈጥሯል ይሉናል አንድሪው ቾውና ቢሊ ፔሪጎ በጋራ በTIME መጽሔት ባስነበቡን መጣጥፍ። በዚህ ቅጽበት እንኳ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ወይም Artificial Intelligence/AI/፤ ሰዓሊውን ተክቶ ረቂቅና ውብ ስዕሎችን እየሳለ፣ ሰዎችን ሆኖ በኢሜል መልስ እየሰጠ፣ ሙዚቀኛውን ሆኖ ሙዚቃን እየቀረጸ ነው።

ወይም ዋና ስራ አስፈጻሚውን ተክቶ ስለ ኩባንያው የዕቅድ አፈጻጸም ለታዳሚው ገለጻ እያደረገ፤ አልያም በኮምፒውተር ኮድ የተፈጠረ ስህተትን ለይቶ መፍትሔ እየሰጠ፤ የሕንጻ ግንባታ ንድፍ እያዘጋጀ፤ ተማሪውን ተክቶ እየተፈተነ፤ ጋዜጠኛውን ተክቶ መጣጥፍ እየጻፈ፤ ለሕመምተኛው የጤና ምክር እየሰጠ፤ ተከሳሹን ተክቶ ጥብቅና ቆሞ ሊሆን ይችላል።

ምን አደከማችሁ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ያልገባበት የሕይወት ቅንጣት የለም ማለት ይቻላል። የመድህኒትንና የቤት ዋጋን ከማውጣት አንስቶ እስከ መኪና መገጣጠምና በማሕበራዊ ሚዲያ የምንመለከተውን ማስታወቂያ እስከ መወሰን ደርሷል። በዚህ ተገርመን ሳናበቃ አዲስ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ወይም Generative AI ወደ ስራ እየገባ ነው ይሉናል እነ አንድሪው በጹሑፋቸው።

ይሄኛው አስተውሎት ጥራትና ጥልቀት ያለው አዲስ ጹሑፍ፣ ምስልና ድምጽ መፍጠር የሚችል ነው። አዲሱ የሰው ሰራሽ ክህሎት ወይም Generative AI ማሕበራዊ ሚዲያ ጥቅም ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ አስገራሚው ቴክኖሎጂያዊ ግኝት ወይም እምርታ ነው። የዚህ ግኝት አካል የሆነው ChatGPT የተሰኘው የደረ ገጽ ማፈላለጊያ ወይም ሰርች ኤንጅን ለምንጠይቀው ነገር ሁሉ ምላሽ መስጠት የሚችል ሰው ሰራሽ አስተውሎት ነው።

ሌላው አዲሱ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ወይም Dall-E የምናልመውንና የምንመኘውን ስዕል መሳል የሚችል ነው። በተለይ ChatGPT ባለፈው ጥር ስራ ላይ ከመዋሉ ከ100 ሚሊየን በላይ ተጠቃሚዎችን በማፍራት፤ ኢንስታግራምና ቲክቶክ ይዘውት የነበረውን ክብረ ወሰን ሰብሯል። በየቀኑ 13 ሚሊየን ደንበኞች እየተጠቀሙበት ይገኛል። በመቶዎች የሚቆጠሩ አዳዲስ እንደ ChatGPT ያሉ የሰው ሰራሽ አስተውሎቶች ወደ ገበያው ለመግባትና ተጠቃሚዎችን ለማፍራት የሞት ሽረት ፉክክር ላይ ተጠምደዋል። ከMidjourney እስከ Stable Diffusion እና GitHub's Copilot ውድድር ላይ ናቸው ይሉናል የመጽሔቱ ጸሐፊዎች።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





# ‹‹ለብሔራዊ ቡድን የሚሆኑ አጥቂዎች ማግኘት ከባድ ነው››

**-አሰልጣኝ ገብረመድህን ኃይሌ**

**ቦጋለ አበበ**

ለ2026 የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ በምድብ አንድ የተደለደለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የመጀመሪያ ሁለት ጨዋታዎቹን ከሳምንት በፊት አከናውኖ በአንድ ነጥብ መመለሱ ይታወቃል። የመጀመሪያውን ጨዋታ ከሴራሊዮን አድርጎ ካለምንም ግብ የተለያየው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን በሁለተኛው ማጣሪያ በቡርኪናፋሶ 3ለ0 ተሸንፏል።

የካፍን መስፈርት የሚያሟላ ስቴድየም ባለመኖሩ ሁለቱንም የሜዳው ላይ ጨዋታዎች በገለልተኛ ሜዳ ያከናወነው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አንድም ግብ ሳያስቆጥር ቀርቷል። ከማጣሪያ ጨዋታዎቹ ጥቂት ቀናት በፊት የዋልያዎቹ አዲስ አሠልጣኝ ሆነው የተሾሙት ገብረመድህን ኃይሌ በአጭር ጊዜ ዝግጅት የዓለም ዋንጫ ማጣሪያ ጅማሬያቸው ተስፋ የሚሰጥ አልነበረም። ከሁለቱ ጨዋታዎች መልስ አሠልጣኙ የሚሰጡት ማብራሪያ ሲጠበቅ የነበረ ሲሆን ከትናንት በስቲያ በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን መሰብሰቢያ አዳራሽ መግለጫውን ሰጥተዋል።




አሠልጣኙ በመግለጫቸው ‹‹በሀገራችን ለብሔራዊ ቡድን የሚሆኑ የአጥቂ ተጫዋቾች ለማግኘት ከባድ ነው።›› በማለት ዋልያዎቹ በሁለቱ ጨዋታዎች አንድም ግብ ሳያስቆጥሩ የተመለሱበትን ምክንያት ተናግረዋል። ይህንን በዝርዝር ሲያብራሩም “ብዙዎቻችሁ የምታውቁት ይመስለኛል አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙ 9 ቁጥሮች አሉ ለማለት እኔ ለእራሴ የማያስደፍረኝ ነው። ግን ያሉትን 9 ቁጥሮች ወደፊት ወስደን ማየት ይጠበቅብናል። ሌላ አማራጭ መውሰድ እንደሚጠበቅብኝ አስባለሁ። እዛ ቦታ ላይ ሌላ ሰው ማለማመድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ያላቸው ቴክኒካል ብቃት ፣ የአጨራረስ አቅማቸው እና የቴክኒክ አረዳዳቸው በየክለቡ ያሉትን 9 ቁጥሮች ስናያቸው ለብሔራዊ ቡድን በጣም አስቸጋሪ ነው። እንደ ሀሳብ የያዝነው እንደ ቡድን ተንቀሳቅሰን ሌላ 9 ቁጥር መፍጠር ካልሆነ እንደዚህ ዓይነት ኳሊቲዎች እየጠፉ ነው ወደፊት የሁላችንም ጥረት ይጠበቃል።” ብለዋል።

‹‹ቡርኪናፋሶ እኛን በ90 ደረጃዎች ይበልጡናል›› ያሉት አሠልጣኝ ገብረመድህን ቢያንስ ቢያንስ ከሁለቱ የማጣሪያ ጨዋታዎች ቡድናቸው ቢያንስ 4 ነጥብ ማግኘት ይገባው እንደነበር ገልፀዋል።

ይሁን እንጂ በመልሶ ማጥቃት የተሻለ ነገር ለማድረግ እንደቡድን መክረን እንደነበር በማስታወስ አጨራረስ ላይ ደካማ መሆናቸው ዋጋ እንዳስከፈላቸው አስረድተዋል። “እኛ ለመከላከል አልገባንም፤ ያለውን ደረጃችንን እናውቀዋለን። ዝግጅታችን እነርሱ በግል ብዙ ነገር ቢኖራቸውም እኛ እንደ ቡድን ተንቀሳቅሰን አንድ ነገር መሥራት እንችላለን የሚል ነበር። አቀራረባችንም ለማሸነፍ ነበር። በዛ መንገድ ነበር የሄድነው ነገር ግን በመጨረሻዎቹ ደቂቃዎች ሦስት ግቦች ተቆጠሩብን። ይህም የሆነው በግል በተፈጠሩ ቀላል ስህተቶች ነው እንጂ እንደ ቡድን ብልጫ ወስደውብን አልነበረም። በግል የሚፈጠሩ ስህተቶችን ደግሞ ለማረም አይቸግርም እንደ ቡድን ተበልጠን ሳንደራጅ ቀርተን ብንሸነፍ ምናልባት ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል። ይሄ ግን በዛ መልኩ አልነበረም።” ብለዋል፡፡

ተጫዋቾቻቸው የስነልቦና ጫና እንደነበረባቸው የገለፁት አሠልጣኝ ገብረመድህን ይህንን ችግር በፍጥነት መቅረፍ ከባድ እንደሚሆን ተናግረዋል።

አሰልጣኙ በመጀመሪያው ጨዋታ በወቅቱ የነበረው አየር ንብረት በጣም ተለዋዋጭ እንደነበር አስታውሰዋል። በዚህም ጨዋታውን ለማቋረጥ ጥያቄ አቅርበው እንደነበር ጠቁመው ፊፋ ጨዋታው እንዲቋረጥ እንዳልፈለገ አብራርተዋል።

አሰልጣኙ ወደ ፊት ቡድኑን ለማጠናከር ከ23 ዓመት በታች ያሉ ተጫዋቾችን መልምሎ እንደ ‘ሻዶ ቲም’ የማዘጋጀት ሀሳብ እንዳላቸው የጠቆሙ ሲሆን፣ የአሠልጣኝ ቡድን አባላትን ቁጥር የመጨመር ሃሳብ እንዳላቸውም አንስተዋል፡፡

“ጠባብ እንደሆነ እናውቃለን። የጊዜ ማነስ ፣ ችኮላ እና ያልተስተካከሉ ነገሮች ነበሩ። ወደፊት የአሠልጣኝ ቡድን አባላትን ሰፋ ለማድረግ እንሠራለን ጊዜ ስለሚኖረን። አንድ ለውጥ ለማምጣት የግድ ብዙ ነገሮችን ማየት አለብን፣ በተለይ የትውልዱ አንድ ቦታ ላይ የመቆም ነገር ይታያል እና ወጣቶችን የምናመጣበት መንገድም አንድ ነገር ነው። ለፌዴሬሽናችን በፕላን ደረጃ የማቀርበው ነገር ይኖራል። ከ23 ዓመት በታች ያሉ ተጫዋቾችን መልምሎ የተወሰነ እንደ ሻዶ ቲም የማዘጋጀት ሀሳብ አለኝ። የፕሪሚየር ሊጉ ወድድር አንድ ቦታ ላይ ስለሚደረግ እነዚህን በየክለቡ የሚመረጡ ልጆች በሳምንት አንዴ እያገኙ ለማብቃት ሰብስበን በተደጋጋሚ እያሠራን ብሔራዊ ቡድኑን የመተካት ሥራ ያስፈልገናል።” በማለት ገልፀዋል፡፡


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁጥር 01/2016

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች ሕጋዊ ድርጅቶችን አወዳድሮ በግልጽ ጨረታ መግዛት ይፈልጋል፡፡
ሎት1፡- የቢሮ የጽህፈት መሣሪያዎችንና አላቂ ዕቃዎች፣
ሎት2፡- የጽዳት ዕቃዎች፣
ሎት3፡-- የመኪና ጎማና ሙሉ ኮንፎርት፣
ሎት4፡- የደንብ ልብስ እና
ሎት5፡- ኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣
በዚሁ መሰረት ከላይ ለተጠቀሱ ዕቃዎች በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች፡-

1. የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ (VAT) ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የዕቃ አቅራቢነት ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
3. ያልታገደ የንግድ ፈቃድ ወይም ታግዶ የነበረ ከሆነ የእገዳ ጊዜውን ስለመጨረሱ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡
4. ተጫራቾች ዋጋቸውን የሚገልፀውን ሰነድ በሰም በታሸገ ፖስታ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን ከቀኑ 11፡30 ድረስ ግ/ፋ/ን/አስ/ር ዳይሬክቶሬት ቢሮ በአካል በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡
5. የጨረታው ሰነድ ይህ የጨረታ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣበት ቀን በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዕለቱ በ4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በቢሮው 1ኛ ፎቅ የግዥ ፋይ/ንብ/አስ ቢሮ ቁጥር 113 ይከፈታል፡፡ ሆኖም 16ኛው ቀን የስራ ቀን በማይሆንበት ጊዜ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው ጊዜና ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
6. ተጫራቾች ለአያንዳንዱ ሎት ከሚያቀርቡት ዋጋ 1% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በባንክ የተረጋገጠ (CPO) ከዋጋ ማቅረቢያው ጋር በጥንቃቄ በሰም በታሸገ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ለእያንዳዱ ሎት ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ግ/ፋ/ን/አስ/ር ዳይሬክቶሬት ቢሮ መግዛት ይቻላል፡፡
8. የተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በራሳቸው ፈቃድ በጊዜው አለመገኘት ሳጥኑን ከመክፈት አያስተጓጉልም፡፡
9. የጨረታው አሸናፊዎች በውሉ መሰረት ግዥ የሚፈጸምባቸውን ዕቃዎች እስከ ዋና ኦዲተር መ/ቤቱ ድረስ በራሳቸው ወጪ አቅርበው ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
10. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
11. የመ/ቤቱ አድራሻ፡- በሀዋሳ ከተማ ሲዳማ ባንክ ዋናው ቢሮ ህንፃ 1ኛ ፎቅ
**ለበለጠ መረጃ** ስልክ ቁጥር፡- +251462127138

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
**ሀዋሳ**